አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3564 | ቅዳሜ መጋቢት 5 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# ለዜጎች ክብር የተሰጠ ዋጋ

"አዲስ አበባ በሰው ተኮር ሥራዎቿ ተምሳሌት ሆናለች"

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**


ፎቶ- ከፋይል
ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በልደታ ክፍለ ከተማ የተገነባውን ዘመናዊ የመኖሪያ ህንፃ ለነዋሪዎች ባስተላለፉበት ወቅት

**በመለሰ ተሰጋ**

"ቅስሙ በገበያ እንዳይፈስ፣ ወንድ ልጅ ብቻውን ነው እሚያለቅስ" እንዲል፣ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን የብሌን አባት ወጣት አሸናፊ አሰፋ "ከዐይኑ ብሌን ጣር ተመጦ፤ ከአንጀት ሲቃ ተቆርጦ" እንዲያ ነው! ለልጁ ሲል የመከራን ዳገት የገፋው፤ የኑሮን ሁዳዴ ያጋመሰው፡፡ አዎ! ሎሬቱ ቀድሞ እንዳመሰጠረው አንጀቱን በአንጀት ነው፣ የታጠቀው፡፡

ይህ ብርቱ አባት እንደሚለው ብሌን፣ ከተወለደች አርባ ቀን ጀምሮ ባጋጠማት የጭንቅላት እክል አልጋ ላይ ውላለች፡፡ "ብሌን ለእኔ ልጄ ብትሆንም ለእግዚአብሔር ደግሞ የእጁ ሥራ ናት። እኔ ሞግዚቷ ነኝ፡፡" ይላል መከራው ቢከብድም ልጅን ማሳደግ የአባትነት ወጉ መሆኑን ሲገልፅ፡፡

ለልጁ ሲል የሹፍርና ሥራውን ትቶ ወደ ፅዳት ሥራ የገባው የብሌን አባት፣ ሁሌም ሌሊት ሌሊት ጨለማና ምድር በወጉ ሳይሰነባበቱ ከቤት ይወጣና፣ ሥራውን አከናውኖ ረፋድ ሦስት

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ወደ ተገልጋዩ የቀረበው አገልግሎት

14


ፎቶ- ከፋይል
ለተንቀሳቃሽ መሶብ አገልግሎት እየተዘጋጁ ያሉ አውቶብሶች በከፊል


## ለዓለም የተረፈ ሀብት

11


ፎቶ- ከገፀ ድር
የፊቼ ጨምበላላ ስርዓት በከፊል

## ስፖርተኞች በፆም ወቅት

20


ፎቶ- ከገፀ ድር
በረመዳን ወር ከፆም ሳይስተጓጎሉ ስፖርታዊ ክዋኔዎችን ከሚያደርጉ ስፖርተኞች ጥቂቶቹ

# ለምርጫው ስኬት ከመራጩ ምን ይጠበቃል?

"መራጩ ምርጫ ባህል መሆን እንዳለበት በማመን መሳተፍ ይኖርበታል"

**የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ደያሞ ዳሌ**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በየቀኑ ምን መስራት፣ ምን መልበስ፣ ምን መመገብ፣ የት መሄድ... እንዳለባችሁ ሌላ ሰው የሚወስንላችሁ ቢሆን ምን ይሰማችኋል? ደስተኛ ትሆናላችሁ ተብሎ አይጠበቅም፡፡ በተመሳሳይ ነጋችሁንም ራሳችሁ ነው መወሰን ያለባችሁ። ነጋችሁ ምን መምሰል እንዳለበት፣ ምን እድል እንዳላችሁ፣ ምን ዓይነት የጤና እና የትምህርት ሥርዓት ማየት፣ በምን ዓይነት ሥርዓት ውስጥ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል


ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ አበባ ነዋሪ ለመምረጥ የሚያስችለውን ካርድ ከምርጫ ጣቢያ እየወሰደ ነው

# ከወንዞቿ የታረቀች ከተማ

"የወንጀለኞች መሸሸጊያና የቆሻሻ መጣያ የነበረውን ስፍራ፤ ውብ፣ ለዐይን ማራኪ እና የቱሪስት መስህብ አድርገን ገንብተነዋል"

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በመለሰ ተሰጋ**


ወንዞች ለብዙ ከተሞች የመኖራቸው ማረጋገጫ የልብ ምት፣ የዜማቸው ማጣፈጫ ቅኝት፣ የፍቅራቸውን ሙዳይ መስሪያ አለላና አክርማ፣ የዕድገታቸውን ጎጆ መቀለሻ ካስማ፣ የብልፅግናቸው መታወቂያ ዓርማ፣ ደህንነታቸውን መጠበቂያ ማማ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

## ርዕሰ አንቀፅ



# የከተማዋ የልማት ፍሬ ማህበራዊ ፍትህን በተግባር እያረጋገጠ ነው!

ልማት የሚለካው በህንፃዎች ርዝመትና በመንገዶች ስፋት ብቻ ሳይሆን፣ በዜጎች የኑሮ ጥራት ለውጥና በሰው ተኮር ሥራዎች ጭምር ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር "ማንንም ወደ ኋላ አንተውም" የሚለውን መርህ በተግባር እያሳየ ይገኛል። ልማት ለሰዎች የተሻለ የመኖሪያ ከባቢና ሰብዓዊ ክብርን የሚሰጥ መሆኑ በተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች እየተረጋገጠ ነው። በተለይም የከተማዋ የኢኮኖሚ እድገትና የኮሪደር ልማት ውጤቶች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎችም ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑ፣ አካታችነቱን የሚያመላክት ነው።

እነዚህ የከተማዋ የልማት ፍሬዎች ማህበራዊ ፍትህን በተግባር እያረጋገጡ ይገኛሉ፡፡ በተለይ ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል፣ ጉለሌ የተቀናጀ የልማት ስራ፣ ማዕድ ማጋራት፣ የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት፣ የተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብር በከተማዋ ማህበራዊ ፍትህን ለማረጋገጥ መሠረት ከሚሆኑ ስራዎች መካከል በጥቂቱ ይጠቀሳሉ፡፡

ለሀገርና ለከተማዋ እድገት ደማቸውንና ላባቸውን ያፈሰሱ፣ ነገር ግን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎችን ማሰብ የመንግስት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም የሞራል ግዴታ ነው። እነዚህ ወገኖች በስተርጅናቸው ለማህበራዊ ቀውስ መዳረግ የለባቸውም። እየደረሰባቸው ካለው ችግር ለመታደግ የከተማ አስተዳደሩ ቀላል የማይባሉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ለአብነትም የቤት ባለቤት እንዲሆኑ የማድረጉ ተግባር ታላቅ ክብርና እውቅና የሚቸረው ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በቅርቡ ባደረጉት ንግግር፣ "የእውነተኛ አመራር ስኬት የሚለካው በታላላቅ ህንፃዎች ግንባታ ብቻ ሳይሆን፣ አቅመ ደካሞች ፊት ላይ በሚታይ እውነተኛ ፈገግታ ነው፤ ዜጎቻችን በገዛ ከተማቸው ባይተዋር እንዳይሆኑና የልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትጋት እንሰራለን" ማለታቸው የመንግስትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። ይህ የርህራሄና የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጉዞ የከተማዋን ገፅታ ከመቀየር ባለፈ የዜጎችን ተስፋ እያለመለመ ይገኛል።

ሰሞኑን በልደታ ክፍለ ከተማ ተገንብተው በችግር ውስጥ ለነበሩ አቅመ ደካሞች የተላለፉት ቤቶች፣ የከተማ አስተዳደሩ የዜጎችን ስቃይ መቅረፍ ላይ ያለውን ቁርጠኝነት እና ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ያሳያሉ። ይህ ተግባር በዜጎች መካከል ያለውን ማህበራዊ ልዩነት በማጥበብ ረገድ የሚጫወተው ሚና የላቀ ነው።

በልደታ ክፍለ ከተማ የተገነባው ዘመናዊ የጂ+4 የመኖሪያ ህንፃ፣ ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ ወገኖች፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ፣ ለአካል ጉዳተኞች እና የሀገር ባለውለታዎች የተላለፈ ሲሆን፣ መንግስት አቅመ ደካሞችን ለመደገፍና የቤት ባለቤት ለማድረግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ማሳያ ነው፤ ተግባሩ የዜጎችን ሰብዓዊ ክብር ከፍ የሚያደርግ ነው፡፡

በከተማዋ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ውበትን ከመጨመር ባለፈ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች ንጹህና ምቹ የመኖሪያ አካባቢ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ትልቅ ለውጥ እያመጡ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

በመሆኑም ይህ አኩሪ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ባለሀብቶችና የንግዱ ማህበረሰብም በዚህ ተግባር ላይ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል። የከተማዋ የልማት ፍሬ ማህበራዊ ፍትህን እንዲያረጋግጥ በማድረግ ረገድ የተጀመረው ስራም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል!

## የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

# ከተማዋን የማይመጥኑ የትራንስፖርት አማራጮች ላይ ትኩረት ቢሰጥ

**ሳሮን ከአራዳ ጊዮርጊስ**

አዲስ አበባ እንደስሟ አዲስ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለተመለከታት ደግሞ እስከዛሬ የት ነበረች? የምትባል ከተማ እየሆነች ነው፡፡ ከተማዋ እያሳየች ያለው ለውጥ ለሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ብቻም ሳይሆን ለሌሎች ሀገራት ከተሞች ጭምር ተምሳሌት እንደሆነች የአደባባይ ሚስጥር ነው። መንገዱ ከስፋት ባለፈ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ታሳቢ ያደረጉ ናቸው፡፡ በመጥፎ ሽታ ይሰነፍጡ፣ ይሰጧቸው ከነበሩ አገልግሎቶች የራቁ፣ ለጤናም ጠንቅ የነበሩ ወንዞቿ አሁን ላይ ተጣብቋቸው የቆየውን አስቀያሚ ገጽታ አውልቀው በመጣል የውበትም፣ የገቢ ምንጭም መሆን ወደሚችሉበት ደረጃ እየተሸጋገሩ ነው፡፡

ይህ አዲስ አበባ ስማርት ሲቲ የመሆን ውጥኗን ማሳካት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወነች የመሆኑ ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም የስማርት ሲቲ ፅንሰ ሀሳብ በውስጡ ከያዛቸው ምሰሶዎች መካከል ስማርት ከባቢ አንደኛው እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

በዚህ ልክ ውብና ሁለንተናዊ ልማት እየተካሄደባት ባለች ከተማ ትራንስፖርቱ ላይ ያለው ክፍተት ግን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ይመስለኛል። በቅርቡ የገጠመኝ ይህንን ለመፃፍ አነሳስቶኛል፡፡ ይህን ስል ግን ሁሉንም ማለት እንዳልሆነ ከግምት ይግባልኝ፡፡

ገጠመኜ በተለምዶ ሚኒባስ የምንላቸው ታክሲ ወይም የትራንስፖርት አማራጭ ላይ ነው። ለግል ጉዳይ ወደ አንድ ስፍራ ለማቅናት የተጠቀምኩት ሚኒባስ ውስጡ ለተሳፋሪው የማይመች፣ ዓመታዊ የትራንስፖርት ፍተሻውን እንዴት አለፈ? የሚያስብል አይነት ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በየመንገዱ በሩ የሚወድቅበትና ሹፌሩ እና ረዳቱ ተጋግዘው መፍትሄ ለመስጠት ጥረት የሚያደርጉበት መንገድ አስፈሪ ነበር። አንዳንድ ታክሲዎች በተለይም ዝናብ በሚጥልባቸው ወቅቶች ከኋላ ወንበር የሚቀመጥ ተሳፋሪ በዝናብ ጠብታዎች የሚበሰብስበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ እኔም በክረምት ወቅት ይህ የገጠመኝ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ መስኮቶች አይደለም ለአደጋ ጊዜ አየር ለማስገባት የማይከፈቱ፤ ውስጣቸው የተበያየደ እና መሰል ችግሮች ነበሩበት፡፡

በታክሲዎቹ ዙሪያ በሆነ አጋጣሚ ስንወያይ አንዱ አጋጣሚውን፣ በሚኒባስ ሲጓዝ የኋላ ወንበር መቀመጥ እንደማይወድ እና ለዚህም በአንድ ወቅት ተሳፍረው ታክሲው የተወሰነ ከተጓዘ በኋላ የኋልኛው በር እንደተከፈተ፣ በወቅቱ አደጋ ባያጋጥማቸውም ከፍተኛ ድንጋጤ እንደፈጠረበት ነገረን፡፡ በሩ የተከፈተው አደጋ ገጥሞት ሳይሆን የታክሲው አሮጌነት እንደሆነ በመገረም ነው ያወጋን፡፡ እነዚህ የተወሰኑ ገጠመኞች ናቸው፡፡ በተለይ አሁን ላይ ሁሉም ባይባልም አብዛኞቹ የሚኒባስ ታክሲዎች ከተማችን እያሳየች ያለችውን ለውጥ እና ተመራጭነት የማይመጥኑ መሆናቸውን በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡

ከተማዋ የሳምንቱን ሰባት ቀናት ሃያ አራት ሰዓት የመስራት ልምምድ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ለዚህ ደግሞ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ሰዎች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ሥራ ገበታቸው እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ ቁጥሩ ቀላል የማይባለው እንደነዚህ አይነት የትራንስፖርት አማራጮችን ይጠቀማል፡፡ በዚህ ሁኔታ ምን ያህሉ በሰዓት በሥራ ቦታው ይገኛል? የሚለውን ማሰብ ተገቢ ነው፡፡

ከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ዘርፉ ላይ እያደረጋቸው ያሉ የተግባር እንቅስቃሴዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው፡፡ ሆኖም እንዲህ አይነት ውስንነቶችም ስላሉ ይህን ማስተካከል ላይ ተገቢውን ትኩረት ቢሰጠው ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች**

**ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ**

**ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ለዜጎች ... ከገጽ 1 የዞረ

ሰዓት ግድም ይመለሳል፡፡ ለምን ቢሉ፣ መናገርም መራመድም እንዳትችል ካደረጋት የህመም ስቃይ ጋር በዝምታ የልጅነት ጊዜዋን እየገፋች ያለች የበኩር ልጁን ሊንከባከብ፡፡

ወጣት አሸናፊ ከአሳዛኝ የሕይወት ምዕራፎቹ መካከል ይህንን ሲያስታውስ ልቡ እያነባ መሆኑን የፊቱ ገፅታ ያሳብቅበታል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፣ የብሌን ታናሽ እህት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ስትገባ ‘ከእህቴ ጋር ካልሆነ ወደ ትምህርት ቤት አልሄድም አለች’ አባት እጅግ ተጨነቀ፡፡ ደግሞም ልጁን በሆነ ነገር ማሳመን እንዳለበት አሰበ፡፡ “አንቺን ትምህርት ቤት ካስገባሁ በኋላ ነው እሷን የማደርሳት” ብሎ አሳመናት፤ እሱ ግን ተደብቆ ከልቡ ፈንቅሎ የወጣውን የእምባ ጎርፍ በጉንጮቹ ላይ አፈሰሰ፡፡

ታዲያ በወቅቱ ይህንን ሁኔታ የሚገልፀው ተንቀሳቃሽ ምስል በማህበራዊ ሚዲያ መሰራጨቱን ተከትሎ ‘አባት ግን እናት መሆን ይችላል ለካ’ የሚሉና መሰል አስተያየቶች በማህበራዊ ሚዲያው ሰሌዳ ላይ ተደጋግመው ተፅፈዋል፡፡

ወጣት አሸናፊ አሰፋ ለአስር ዓመት የአልጋ ቁራኛ የሆነች ልጁን፣ አቅመ ደካማ እናቱን እና እህቶቹን የብሌንንም ታናሽ እህት በተከራያት ጠባብ ቤት ውስጥ ዓመታትን በስቃይ አሳልፏል፡፡

ዛሬ ግን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይህንን ታሪክ ቀይሮታል፡፡ በልደታ ክፍለ ከተማ ሳር ቤት አካባቢ ከተገነቡ ዘመናዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ አንዱን ለብሌን አባት አበርክቷል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ብሌን፣ የተሻለ ህክምና የምታገኝበትንም ዕድል አመቻችቷል፡፡

ባሳለፍነው ረቡዕ (መጋቢት 2 ቀን 2018 ዓ.ም) በልደታ ክፍለ ከተማ የተገነባው ዘመናዊ የመኖሪያ ህንፃ፣ ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ ወገኖች፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ፣ ለአካል ጉዳተኞች እና የሀገር ባለውለታዎች ተላልፏል፡፡ በዚሁ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክት፣ በልደታ ክፍለ ከተማ የገነባነውን ዘመናዊ የጂ+4 የመኖሪያ ህንፃ፣ ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ ወገኖች፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ፣ ለአካል ጉዳተኞች እና የሀገር ባለውለታ ለሆኑ ነዋሪዎቻችን በክብር ማስተላለፋቸውን ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ የልማት ሥራዎች ለተነሱ፤ በቀበሌ ቤት ውስጥ በደባልነት፣ በጥገኝነትና በላስቲክ ቤት ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ እንዲሁም የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ በላያቸው እያለፈ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩ ወገኖቻችን ጭምር ቤት አስረክበናል ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ አዲስ አበባ በሰው ተኮር ሥራዎቿ ተምሳሌት እንደሆነችም ተናግረዋል፡፡

አክለውም ሰው ተኮር ሥራዎችን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስጀምረው መመሪያ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 7 ዓመታት በሰው ተኮር እሳቤያችን እና በበጎነት አገልግሎት ተሳትፎ ከ45 ሺህ በላይ ቤቶችን ለአቅመ ደካሞች መገንባት ችለናልም ብለዋል።

በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበር በ4 ወራት አጭር ጊዜ ውስጥ የተገነባው ይህ የመኖሪያ ቤት፣ 5 ነባር ቤቶችን በማንሳት 70 አባወራዎች ቤት እንዲያገኙ ያደረገ ነው። ይህም ከእጦት መንፈስ ወጥቶ ቦታን በአግባቡ በመጠቀም ትልቅ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል የሚያሳይ መሆኑን የጠቀሱት ከንቲባዋ፣ ግንባታውም የጥራት ደረጃውን የጠበቀ፣ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ፣ የዜጎችን ክብር የሚመጥንና የቤት ቁሳቁስ የተሟላለት ዘመናዊ ህንፃ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በልደታ ክፍለ ከተማ የተገነባውን ዘመናዊ የመኖሪያ ህንፃ ለነዋሪዎች ባስተላለፉበት ወቅት

> “ባለፉት 7 ዓመታት በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳትፎ ከ45 ሺህ በላይ ቤቶችን ለአቅመ ደካሞች መገንባት ተችሏል”

አክለውም፣ ከተማችን ለሁላችንም ትበቃለች፤ መተሳሰብና ፍቅር ካለ ደግሞ ይበልጥ መስራት ይቻላል። በቀጣይም ለብዙዎች ለመድረስ በትጋት እንሰራለንም ብለዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የቤት ችግር ዓለም አቀፋዊ ነው፡፡ ለአብነትም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ ጥቅምት 20 ቀን 2023 በኒው ዮርክ ከተማ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ “UN expert urges action to end global affordable housing crisis” በሚል ርዕስ ሰፋ ያለ ጥናት በዘርፉ ባለሙያዎች ቀርቦ ነበር፡፡ በዚህ ጥናታዊ ሪፖርት መሠረትም በዓለማችን ቤት መስራት አሊያም መግዛት የማይችሉ ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ ነው፡፡

ይህንንም ተከትሎ በዓለማችን በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የመኖሪያ ቤት ወጪያቸውን መክፈል ባለመቻላቸው ብቻ ከቤት ንብረታቸው እንደሚፈናቀሉ፣ ይህም ለቤት እጦት መባባስ አስተዋጽኦ ስለማድረጉም በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

በመሆኑም በዓለም ዙሪያ 1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ህዝብ በቂ የመኖሪያ ቤት እና መሠረታዊ አገልግሎቶች እንደሌለው የጠቆመው ሪፖርቱ ይህም በ2030 ወደ 3 ቢሊዮን ሊደርስ እንደሚችል በሪፖርቱ ተጠቁሟል፡፡

በመሆኑም ይላል በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበው የባለሙያዎች ጥናታዊ ሪፖርት “አስተዳደሮች፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች እና ተቋማት የመኖሪያ ቤት እጥረትን ለመፍታት የበለጠ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ አለባቸው” ይላል፡፡

በዓለማችን የተለያዩ አካባቢዎች አሳሳቢ የሆነው የቤት ችግር በአዲስ አበባ ከተማም የሚታይ ስለመሆኑ ከላይ ካነሳናቸው ሀቆች ባሻገር ብዙ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህንን በውል የተረዳው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም በጋራ መኖሪያ ቤቶች ከሚያከናውነው ቤቶች ግንባታ በተጨማሪ የተለያዩ ባለሀብቶችን እና በጎ ፈቃደኛ ዜጎችን በማስተባበር አዳዲስ ቤቶችን በመገንባትና ሊወድቁ የደረሱ ደሳሳ ጎጆዎችን በአዲስ መልክ ቀና በማድረግ የበርካቶችን እምባ እያበሰ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉት በወራቤ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር አንዋር ጫሚሶ እንደገለፁት እንዲህ አይነት ሰው ተኮር ተግባራት ማህበራዊ መስተጋብሩን እውን ለማድረግ እንደሚያግዙና የሀገሪቱን ልማት በተሻለ መሠረት ላይ ለማንበርም ትልቅ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ እንደሚሉት ብልፅግናን ለማረጋገጥ እንደ ሀገር ከተቀመጡት የዘላቂ ልማት ግቦች መካከል አንዱ አካታች የሆነ እድገት ማምጣት ነው፡፡ ይሄውም ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን ወይም ለተለያዩ ማህበራዊ እና መሰል ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካታች በሆነ መልኩ መስራት ሀገራችን አሁን የምታደርገውን ጥረት ሙሉ ለማድረግ ያግዛልም ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል ይህን መሰል ተግባራት ላይ ተሰማርተው የምናያቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ነበሩ ያሉት የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ አሁንም ቢሆን እነዚህ ተቋማት በተለያዩ ሀገሪቱ ክፍሎች ያሉ ቢሆንም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ትልልቅ ከተሞች የሚታዩ ማህበራዊ ችግሮችን ይሸፍናሉ ማለት አይቻልም፡፡ ለአብነትም አዲስ አበባ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለስራ ዕድል፣ ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ እና በሌሎች በርካታ ጉዳዮች የሚፈልሱባት ከተማ ናት፡፡ በመሆኑም መንግስት ይህንን ጉዳይ ትኩረት በመስጠት መሥራቱ በጣም ትልቅ ነገርና እንደ ሀገርም ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል ተግባር ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ችግሮች ለመቅረፍ እየተሰሩ ያሉ ዘርፈ ብዙ ልማቶች የሚበረታቱ መሆናቸውን የጠቆሙት የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ አንዋር ጫሚሶ፣ ይህን መሰል ተግባር በቀጣይነት መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥረት ማድረግና ማገዝ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ሶፎንያስ ፍሰሃ በበኩላቸው፣ ከተማዋ በተስፋ ብርሃን እና በተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብር፣ በቤቶች ዕድሳት እና ለተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሚዘጋጁ የማገገሚያ ማዕከላት የተጋላጭ ወገኖችን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

ባሳለፍነው ረቡዕ በልደታ ክፍለ ከተማ ከተገነባው ዘመናዊ የጂ+4 የመኖሪያ ህንፃ፣ የቤት ባለቤት ተጠቃሚ ከሆኑ የመዲናዋ ነዋሪዎች መካከል ወይዘሮ መስከረም ሰለሞን አንዷ ናቸው፡፡ ትናንት እንደነገሩን በተቀለሰች ከላይም ከታችም በምታፈሰው በዚያች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የስቃን ገፈት የመከራን ዳገት መውጣትና መውረዳቸውን ሲያስታውሱ የሚያቃጥል የሀዘን እንባ በጉንጫቸው በረንዳ ይፈስሳል፡፡ ችግራቸውን በውል ተረድቶ ከተማ አስተዳደሩ የሰጣቸውን የዛሬውን ውብና ምቹ ቤት ሲያስቡ ደግሞ ከሀዘን ስሜታቸው ድንገት ይወጡና ደስታቸው ወደር እንደሌለው የፊታቸው ገፅታ ከቃላት በላይ ይናገራል፡፡

# ከወንዞቿ ... ከገጽ 1 የዞረ

እና ስልጣኔያቸውንም ማሳያ መስታወት ናቸው፡፡

ለዚህ ደግሞ የምድራችንን ውብ ከተሞች የታሪክ መዝገብ ስንገልጥ እና የዛሬ ዝናቸውን ስናደምጥ ይህንን እውነት እናገኛለን፡፡ “የሀገር ፀጋ የሀገር ልብስ” እንዳለችው ድምፃዊት እጅጋየሁ ሽባባው፣ የዓባይ ወንዝ ለካርቱም፣ ካይሮና አሌክሳንደሪያ ከተሞች የውበታቸው ሰገነት፣ ምግብና መጠጣቸው ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ ለኢትዮጵያ ልብሷም ጉርሷም መሆኑ ሳይዘነጋ፡፡

ወደ አውሮፓ ከፍ ብንልም የቴምዝ ወንዝ የለንደን ታሪክ እና ባህል ዓርማ ነው። ከ321 ኪሎ ሜትር በላይ የሚሸፍነው ይህ ወንዝ ከተማዋን እያረሰረሰ፣ ፈገግታን በፊቷ ላይ እየነሰነሰ እና ደስታዋን እየጨመረ በስስት እያያት አቋርጧት ያልፋል፡፡

በወንዙ ዳር ያሉ ፓርኮች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ መሰል የሰውን ልጅ በሀሴት የሚያረሰርሱ መናፈሻዎች ለለንደን ከተማ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ለጐብኝት፣ ለስብሰባና ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ወደ ከተማዋ ለሚመጡ እንግዶች ተመራጭ መዳረሻዎች፣ ጭንቀትና ናፍቆትን ማስረሻዎች እና ተበልቶ የማያልቅ የልቡና ማዕድ ናቸው፡፡

በአምስተርዳም የአምስቴል ወንዝ ለከተማው የውበት ምንጭ ነው፤ በወንዞቹ ዳርና ዳር ያሉ ታሪካዊ ሕንፃዎች እና ድንቅ ስፍራዎች በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጎብኚዎችን የሚስብ ልዩ ውበትን ፈጥረዋል። የአምስቴል ወንዝ ለከተማዋ የውበት ምንጭ ብቻ አይደለም፤ ከጫፍ እስከ ጫፍ መመላለሻና ካሰቡት መድረሻ መንገድም እንጂ፡፡

የሞስኮቫ ወንዝ በሞስኮ እምብርት ውስጥ የተንሰራፋ እና የከተማዋን የህንፃ ጥበብ በውሃ መስታወትነት የሚያሳይ ድንቅ ፀጋዋ ነው፡፡ የወንዙ ዳርቻዎች በመናፈሻ ቦታዎች፣ በእግረኛ መንገዶች እና በባህላዊ ተቋማት የተሞሉ በመሆናቸው ከተማዋን የእንቅስቃሴ ማዕከል አድርጓታል፡፡ ይህ ወንዝ በደማቋ ከተማ ውስጥ በተፈጥሮ እና በከተማ ህይወት መካከል ያለውን ጣፋጭ መስተጋብር የሚያሳይ ዋቢ ምስክርም ሆኖ ያገለግላል፡፡

እውቋ ብራዚላዊት የስነ ሕንፃ እና የከተማ ፕላን ተመራማሪ ቲፋኒ ኒኮሊ፣ ‘The value of urban rivers: European experiences and a South American perspective’ በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ ጽሑፋቸው እንደገለፁት፣ በብዙ የአውሮፓ ዋና ከተሞች ያሉ ወንዞች የውበት፣ የሀብት፣ የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን የዓሳም፣ የሀሳብም መመላለሻ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ በፓሪስ፣ በለንደን፣ በስቶክሆልም፣ በኦስሎ እና መሰል ከተሞች ያሉ ወንዞችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ወንዞች ለዓለማችን ታላላቅ ከተሞች የውበትም የሀብትም ምንጭ እንደሆኑ አያሌ አብነቶችን መጥቀስ ብንችልም፣ አዲስ አበባ ከተማና ወንዞቿ ግን ለዚህ የታደሉ አልነበሩም፡፡ ከአዲስ አበባ ወንዞች የሚፈልቀው ደስ የማይል ሽታ



ፎቶ- ከፋይል

የቀድሞው የቁርጡሚ ወንዝ ገፅታ በከፊል



ፎቶ- ከፋይል

በወንዝ ዳርቻ ልማት ያሸበረቀው የቁርጡሚ ወንዝ አሁናዊ ገፅታ በከፊል

በውሃ ውስጥ ከፍተኛ ብክለት መኖሩን የሚያሳይ እንደሆነ ተደጋግሞ የተነገረ ሀቅ ነው፡፡ ይህ መጥፎ ሽታ የከተማዋን ገጽታ ከማበላሸት አልፎ የህብረተሰብ ጤና ጠንቅ ስለመሆኑም ምስክር አያሻውም፡፡

መዲናዋ ግን የወንዝ ሀብታም ናት፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአዲስ አበባ 7 ትልልቅና ከ76 በላይ ትንንሽ ወንዞች ቢኖሩም ለከተማዋ ውበትና ሀብት መሆን ግን አልቻሉም ነበር፡፡ ከታላላቅ ወንዞቿ መካከልም ቀበና፣ ባንተይቀጡ፣ ቀጨኔ፣ ቁርጡሚ፣ ቡልቡላ፣ አቃቂ እና የቄራ ወንዞችን መጥቀስ በቂ ነው፡፡

በመዲናዋ የተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት ግን የአዲስ አበባ ወንዞችን ወደ ሞት ሳይሆን ወደ ውበት፣ ወደ ብክለት ሳይሆን ወደ ሀብት እንዲፈስሱ የሚያደርግ ዕድል እንደሆነም ብዙዎች በመመስከር ላይ ናቸው፡፡

ለአብነትም ባሳለፍነው ማክሰኞ አመሻሽ ላይ በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ እጅግ ዘመናዊ ሆኖ የተገነባው የድል ፕላዛ እና የቁርጡሚ የወንዝ ዳርቻ ልማት ተመርቋል፡፡ በዚሁ ወቅት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክት “በአንድ ወቅት የወንጀለኞች መሸሸጊያና የቆሻሻ መጣያ የነበረውን ስፍራ ዛሬ ውብ፣ ለዐይን ማራኪ እና የከተማችን አንዱ የቱሪስት መስህብ አድርገን ገንብተነዋል።” ብለዋል፡፡

የአፍሪካ ልማት ባንክ “Addis Ababa Beautifying Sheger River Development Project” በሚል ርዕስ ጥቅምት 17 ቀን 2022 እ.ኤ.አ. ይፋ ባደረገው ጥናታዊ መረጃ መሰረት ቁርጡሚ እና የቀበና ወንዞች ጥቅጥቅ ባሉ ሰፈሮች ልብ ውስጥ የሚፈስሱ ናቸው፡፡ በዚያው ልክ ከመኖሪያ ቤቶች እና ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ቆሻሻዎች የወንዞቹን ተፈጥሯዊ መልክና መዓዛ ቀይረውት ለብዙዎች የጤና እክል ምክንያት ከመሆናቸውም ባሻገር፣ በዙሪያቸው የሚኖሩ ሰዎች በዝናብ ወቅቶች ለከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ይጋለጡ እንደነበርም በመረጃው ተመላክቷል፡፡

“ዓሳ አበላሻለሁ ዓባይ ዳር ነው ቤቴ…” እንዲል የሀገሬ ሰው፣ ‘ቁርጡሚ’ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ዓሳ ማለት ሲሆን፣ ምንም

“የቁርጡሚ ወንዝ ዳርቻ ልማት 2 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን፣ የተለያዩ የሕዝብ አገልግሎት መስጫዎችን፣ የሕፃናት እና የአዋቂዎች ስፖርት ማዘውተሪያዎችን አካትቶ በጽዱና በቆንጆ ሁኔታ ተገንብቷል”

ተጨማሪ መረጃ ሳያስፈልገን ይህ ወንዝ ዓሳዎች እንደልባቸው የሚፈነጩበት፣ በዘመኑም የአካባቢው ነዋሪዎች ምግብና መጠጣቸውን የሚያገኙበት የሜዳ ላይ ማጀት ነበር ማለት ነው፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ባሳለፍነው ወር ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረትም በኢትዮጵያ እየተከናወነ ያለው የወንዝ ዳርቻ ልማት የወንዝ ተፋሰሶችን ከብክለት አጽድቶ ማከም እና መልሶ ህያው ከማድረግ ባሻገር፣ በታየ ሁሉን አቀፍ ርዕይ የተመራ ነው። ይህ አሰራር በወንዝ ዳርቻዎች የመሠረተ ልማቶችን በማስተሳሰር ላይ ያተኩራል። በሁለቱ አቅጣጫ የወንዝ ዳርቻዎች እንደየሁኔታው 50 ሜትር የመተንፈሻ እና መናፈሻ ዞኖች የተሰናዱበትም ነው። በእነዚህ ኮሪደሮች ያለውን የመሬት አጠቃቀም በማደራጀት ብክለትም ሆነ የጎርፍ ስጋትን ለማስወገድ በሚያስችል ሁኔታ ተሰርቷል። የቀደመውን ሥነ ምኅዳር ለመመለስ፣ ህዝባዊ ስፍራዎችን ለመገንባት፣ የመንቀሳቀሻ መንገዶችን ለማቆራኘት ብሎም የኢኮኖሚ እድሎችን ለማስፋት ጥረት ተደርጓል። ይህ እንደየተጨባጭ ሁኔታው በመለዋወጥ እና ምሉዕነት ባለው እይታ የተፈፀመ ዘዴ የወንዝ ዳርቻዎችን ዘላቂ የከተማ ልማትን እና የማኅበረሰብ ደኅንነትን የሚደግፉ፣ በሚገባ የሚመሩ፣ ምርታማ፣ ለኑሮ የተመቹ ከባቢዎች አድርጓቸዋል።

ለዚህ ደግሞ በአዲስ አበባ ከቀበና ድልድይ እስከ እንጦጦ ተራራ ያለው የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ባሳለፍነው ማክሰኞ የተመረቀው የቁርጡሚ የወንዝ ዳርቻ ልማት በቂ ምስክር ናቸው፡፡ 2 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የቁርጡሚ የወንዝ ዳርቻ ልማት የተለያዩ የሕዝብ አገልግሎት መስጫዎችን፣ የሕፃናትና የአዋቂዎች ስፖርት ማዘውተሪያዎችን አካትቶ በጽዱና በቆንጆ ሁኔታ ተገንብቷል።

ፕሮጀክቱ የህፃናት መጫወቻ፣ የስፖርት ሜዳ፣ 5 አምፊ ቴአትር፣ የህፃናት ማቆያ (daycares)፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች፣ ወደ ጎላ ሚካኤል የሚሻገር ድልድይ እና 4 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ ማካተቱን የጠቀሱት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ ስለ ከተሜነት ስናወራ የተሳለጠ መሰረተ ልማት ያለው፣ የህዝብ የጋራ መገልገያ ስፍራዎች ያሉት፣ የስራ እድልን የሚፈጥር ንፁህ፣ ውብ፣ ምቹ መኖሪያ እና ጤናማ አካባቢን መፍጠር እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉት የጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝምና መስተንግዶ ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር ደመቀ ክብሩ እንደገለፁት፣ የኮሪደር ልማቱ በመዲናዋ የተገነቡ የቱሪዝም መስህቦችን በማገናኘትና የጎብኚዎችን እንግልት በመቀነስ ከተማዋን በጎብኚዎች ተመራጭና ዓለም አቀፍ የቱሪዝም መዳረሻ እያደረጋት ነው፡፡

በተለይም እንደ ለንደን፣ አምስተርዳም እና ፓሪስን የመሳሰሉ ከተሞች የውበታቸው ምንጭ ወንዞቻቸው ናቸው። ለዓለማችን ውብ ከተሞች ወንዞች በወርቅና በእንቁ እንደተሰራ አንገት ሀብል ደምቀው የሚታዩባቸው እና በርካታ የቱሪዝም ፍሰትን የሚጨምሩባቸው የውበትም የገቢም መሰረት ናቸው። በመሆኑም በአዲስ አበባ ወንዞች ላይ እየተሰራ ያለው ልማት የከተማዋን ሁለንተናዊ ከፍታ እየጨመረው እንደሆነም ነግረውናል፡፡

የሀገሬ ሰው ወዳጁን ሲመርቅ “እደረጃው ድረስ“ ይላል፡፡ እውነት ነው፤ ከፍ ካለው መድረስ ልብ ያሞቃል። ህይወትን ያደምቃል፡፡ የሆነ ሆኖ ዛሬ የብዙዎች ትዝታ ወደሆነው ቁርጡሚ ወንዝ በአካል ተገኝቻለሁ፡፡ ወንዙን ልክ እንደ እኔ በወጉ ለተመለከተው ትናንትን፣ ዛሬን እና ነገን እንደ መፅሐፍ ተገልጦ፣ እንደ አንበሳ ደረቱን ገልብጦ፣ እንደ ጠቢብ ስለ እውነት አምጦ፣ እንደ ለጋስ ሳይሰስት፣ እንደ ዋሾ ሳይወሰልት፣ ትናንትን በዛሬ፣ ዛሬንም በነገ መነፅር እያስመለከተ ታሪክን ከነ ድፍድፉ ያጠጣናል፡፡ “ጥንት ዓሳዎች እንደ ቀይ ባህር መርከቦች የሚርመሰመሱብኝ፣ ሰዎች ደስታቸውን የሚያጣጥሙብኝ፣ ትናንት ደግሞ ጀርባቸውን ሰጥተው ቆሻሻቸውን የሚወረውሩብኝ ነበርኩ፤ ዛሬ ደግሞ እንደ ጥንቱ አምሮብኛል” ይላል፡፡

## ለምርጫው ... ከገጽ 1 የዞረ

መኖር እንደምትፈልጉም በራሳችሁ መወሰን ትፈልጋላችሁ። በምርጫ መሳተፍን አስፈላጊ የሚያደርገው ይህ ምክንያት እንደሆነ “የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለፍትሐዊ ምርጫና ዴሞክራሲ” የተሰኘውን ተቋም በሥራ አስፈጻሚነት የመሩት እና የምርጫ ጉዳይ ባለሙያዋ ኑኖ ዶልዲዝ ይናገራሉ፡፡

“Your vote, your voice: why every vote matters” በሚል ርዕስ “UN Today” በተሰኘው የገፀ ድር ጋዜጣ ላይ ዶልዲዝ በሰጡት ማብራሪያ፣ “ምርጫ መኖር የምንፈልግባትን ዓለም በመወሰን ወይም ተፅዕኖ በማሳረፍ ጉልህ ፋይዳ አለው። አንዳንዶች የአንድ ሰው ድምፅ ምንም ለውጥ አያመጣም ይላሉ። ነገር ግን አስር ሰዎች ወይም መቶ ሰዎች ተመሳሳይ ነገር ቢያስቡስ? ይህ ማለት አስር ድምፅ ወይም መቶ ድምፅ ባከነ ማለት ነው። በታሪክ ውስጥ የአንድ ሰው ድምፅ የውሳኔውን ውጤት የለየባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። ስለዚህ ያቺ ወሳኝ ድምፅ ያንተ/ያንቺ ልትሆን ትችል ነበር” ይላሉ፡፡

በኢትዮጵያም 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ለዚህም በምርጫው የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመወዳደሪያ ምልክትና ማንፌስቷቸውን እያስተዋወቁ ነው። በተለያዩ ጉዳዮች ላይም በመገናኛ ብዙኃን ክርክሮችን እያካሄዱ ይገኛል። ከየካቲት 28 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የመራጮች ምዝገባ ጀምሯል፡፡ ከዚህ አኳያ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ፣ ነጻና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲካሄድ ከሕዝብ ምን ይጠበቃል? ስንል የከተማዋን ነዋሪዎች፣ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና መረጃዎችን በማካተት ለመዳሰስ ሞክረናል፡፡

“ምርጫ የሕዝብን ጥያቄዎች የሚመልስና ሀገርን በቀጣይ አምስት ዓመት የሚመራ አካልን የምንወስንበት ጉዳይ በመሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሕዝብን ጥያቄዎች ለመመለስ አዳዲስ ሐሳብና አጀንዳ በመያዝ የሚቀርቡበትና ከዚህ ውስጥ የተሻለ ሀገርን የሚያራምድ ሐሳብ ያለውን የምንመርጥበት ነው” ይላሉ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት ነዋሪ የሆኑት አቶ ጉዲና አበሽሎ፡፡

ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ምርጫዎች በመራጭነት ለአራት ጊዜ ያህል መሳተፋቸውን የነገሩን አቶ ጉዲና፣ በዘንድሮው ጠቅላላ ምርጫ ድምፅ ለመስጠት ዝግጅት እያደረጉ ይገኛሉ። በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚዲያ እያካሄዱት ያለውን የምርጫ ክርክር እየተከታተሉ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው አስተያየቱን ያጋራን ወጣት በረከት አበራ ይባላል፡፡ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ነዋሪ ነው፡፡ ወጣቱ እንደሚናገረው፣ ምርጫ በሕዝብ ድምፅ አሸናፊ ሆኖ ሀገርን የሚያስተዳድር አካል የሚመረጥበት ወሳኝ ሂደት በመሆኑ ካርድ በማውጣት ድምፅ መስጠት እንደ ዜጋ ኃላፊነትን መወጣት ነው፡፡ የአንድ ሰውም ድምፅ በምርጫ ዋጋ አለው፡፡

በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ መሳተፉን የሚናገረው ወጣት በረከት፣ “በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫም ‘ይጠቅመኛል፤ ለሀገርና ሕዝብ ይበጃል፤ ሀገርን ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ይሠራል’ የምለውን የፖለቲካ ፓርቲ ለመምረጥ ተዘጋጅቻለሁ። ለዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ፖሊሲና ፕሮግራም ይዘው እንደቀረቡ በቴሌቪዥን መስኮትና በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ የፓርቲዎች የክርክር መድረኮችን እየተከታተልኩ ነው፡፡ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅም ከገዥው ፓርቲ ባለፈ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራትና ሕዝቡ ከሁሉም በላይ ሰላምን በማስቀደም መንቀሳቀስ ይገባቸዋል” ሲል ሐሳቡን አጋርቷል፡፡

ሌላው የአካባቢው ነዋሪ የሆኑት አቶ ረሻድ አብደላህ እንዲሁ ምርጫው “በሕይወታችን የተሻለ ለውጥ ያመጣልናል” ብለን የምናስበውን የፖለቲካ ፓርቲ በመምረጥ ኃላፊነት የምንሰጥበት ነው፡፡ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ድምፅ ለመስጠትም ከወዲሁ በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ የምርጫ ፉክክሮችን እየተከታተሉ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

አቶ ደያሞ ዳሌ ግሎባል ፒስ ባንክ በተሰኘ በሰላም ግንባታ ዙሪያ በሚሠራ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም የሰላም ግንባታና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር እና የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁር ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚናገሩት፣ ምርጫ የአንድ ሀገር ዜጎች የሚያስተዳድራቸውን፣ ሕግ የሚያወጣላቸውን፣ የሚወስንላቸውን ሰዎች የሚመርጡበትና የሥልጣን ባለቤት መሆናቸውን የሚያሳዩበት ሂደት ነው፡፡ ምርጫ የሚካሄደው ሰላማዊና ተአማኒነት ያለው የፖለቲካ ሽግግር ሂደት እንዲኖር ነው፡፡ ምርጫ ለማካሄድ ሰላም ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ በምርጫው የሚሳተፉ ተዋናዮች ምርጫን በተመለከቱም ሆነ በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች መሠረት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡

አቶ ደያሞ እንደሚሉት፣ በምርጫ ድምፅን መስጠት የዜግነት ግዴታ ሆኖ መታየት አለበት፡፡ ለዚህም ሕዝቡ የምርጫ ካርዱን መውሰድና ድምፁን ለመስጠት ዝግጁ መሆን ይኖርበታል፡፡ የምንተቸውን፣ የምንወቅሰውን ለመቀየር ወይም ጥሩ ሠርቷል ወይም የተሻለ ሐሳብ አለው ብለን የምናምንበትን ለመደገፍ ምርጫ ወሳኝ ነው፡፡ ምርጫ ተጠያቂነትን ለማምጣት ያስችላል፡፡ ለዚህም ሁሉም ዜጋ በነቂስ በመውጣት የዜግነት ጉዳይ አድርጎ የምርጫ ካርድ መውሰድ አለበት።

ሌላው ከሕዝብ የሚጠበቀው በምርጫው የሚወስነው ውሳኔ በእውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የፓርቲዎችን አቋም ማወቅ ነው፡፡ ለዚህም የምርጫ የክርክር መድረኮችን መከታተል ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁ በደፈናው ድምፅ ከመስጠት ይልቅ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸውን ፖሊሲና ስትራቴጂ በመረዳት የተሻለ የሚለውን በማነጻጸር መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ‘ይህን ፓርቲ የምመርጠው በዚህ ምክንያት ነው፤ አቋሙ ይኼ ነው’ ለማለት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምሳሌ በትምህርት፣ በውጭ ጉዳይ፣ በጤና እና በተለያዩ ጉዳዮች ያላቸው ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የምርጫ ማኒፌስቷቸውን፣ እርስ በርስ የሚያደርጉትን ክርክርና ፉክክር መከታተል እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመገናኛ ብዙኃን ባሻገር በቀጣይ በየቦታው በመንቀሳቀስ የሚያደርጉትን የምርጫ ቅስቀሳ መከታተልም ከሕዝብ ይጠበቃል። መራጩ ምርጫ የሰላም መሠረት መሆኑን፣ ሰላማዊ ፖለቲካ እንዲፈጠር ምርጫ ባህል መሆን አለበት የሚለውን በማመን መሳተፍ እንዳለበት አቶ ደያሞ ያነሳሉ፡፡

“በምርጫው ላይ በማህበራዊ ሚዲያ የተለያዩ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ አስተያየቶች ሊሰነዘሩ፤ ብዙ ግርግሮችም ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ዋናውና ወሳኙ መሬት ላይ የሚሠራው ነው። ከዚህ አኳያ ሕዝቡ ከአሉባልታዎች ራሱን በመጠበቅ ምርጫው ሰላማዊ፣ ነጻ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ መወጣት ይኖርበታል፡፡ ሀገር ሰላም የምትሆነው፤ ብዙ ነገር የምናስተካክለው የምርጫ ሥርዓቱን ስንቀበል ነው፡፡ የሚጎድለንን ነገር እያሟላን እንሄዳለን፡፡ በምርጫ ካልተሳተፍን የምናመጣው ለውጥ የለም። ምርጫ የሰላም መሠረት ነው፡፡” ሲሉ ምሁሩ አክለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ምርጫ የሚካሄደው በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ለምሳሌ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሆነ በ100 ሺህ ሕዝብ አንድ የሚወክል ሰው ለመምረጥ ነው፡፡ “የእኔ ድምፅ አንድ ቦታ ብቻ ነው ዋጋ የሚኖረው፤ ሌላ ቦታ የሚያሸንፈውን የሚወስነው ሌላው መራጭ ነው” በማለት ከምርጫ ራስን ማግለል አይገባም፡፡ እያንዳንዱ ድምፅ ዋጋ አላት፡፡ የምንፈልገው እንደሚያሸንፍ አምነን ብቻም ሳይሆን ‘ድምፄ ዋጋ አለው፤ ኃላፊነቴን ተወጥቻለሁ’ በሚል ተረድተን ድምፅ መስጠት እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ አበባ ነዋሪ ለመምረጥ የሚያስችለውን ካርድ ከምርጫ ጣቢያ እየወሰደ ነው

> **“የምንተቸውን፣ የምንወቅሰውን ለመቀየር ወይም ጥሩ ሰርቷል ወይም የተሻለ ሐሳብ አለው ብለን የምናምንበትን ለመደገፍ ምርጫ ወሳኝ ነው። ምርጫ ተጠያቂነትን ለማምጣት ያስችላል። ለዚህም ሁሉም ዜጋ በነቂስ በመውጣት የዜግነት ጉዳይ አድርጎ የምርጫ ካርድ መውሰድ አለበት”**

# በፆም ወቅት የሚገለጡ በጎ እሴቶች

**በሄለን ጥላሁን**

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው የክርስትና እና እስልምና እምነት ተከታዮች እንደየ ዕምነታቸው በፆምና በፀሎት ወደ ፈጣሪ ልመናቸውን የሚያቀርቡበት ወቅት ላይ ይገኛሉ። ይህንንም አጋጣሚ መነሻ በማድረግ "በአጿማት ወቅት ተግባራዊ የሚደረጉ እሴቶችን ለሀገር በሚበጅ መልኩ እንዴት ማጠንከር ይቻላል?" በሚለው ዙሪያ የሚከተለውን ጽሑፍ አጠናቅረናል፡፡


ፎቶ- ከፋይል
መላከታቦር መምህር ኢያሱ ሲሳይ


ፎቶ- ከፋይል
ኡዝታዝ አቡበከር አህመድ


ፎቶ- በገነት ወንድሙ
መጋቢ በለጠ ኃጃሎ

መላከታቦር መምህር ኢያሱ ሲሳይ ይባላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በአያት ደብረ ሰላም ዋሻ ቅዱስ ሚካኤል እና በአቡነሃራ ድንግል ማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ናቸው፡፡ "አንድ አማኝ ፆም በመፆሙ የሚያገኛቸው ስጋዊ ብሎም መንፈሳዊ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?" ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ በሰጡን ምላሽ፤ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ፆም መፆም ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ ነገር ስለመሆኑ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ የሰው ልጅ ከፈጣሪው ዘንድ እንዲሆንለት የሚፈልገውን ጉዳይ በፆምና በፀሎት ይጠይቃል፡፡ አሁን ያለንበት የአብይ ፆምም ታላቁ ጾም በመባል ይታወቃል። እራስን በማዋረድና ዝቅ በማድረግ ልመናና ፀሎትን ለፈጣሪ የምናደርስበት ወቅት ነው" በማለት አብራርተዋል፡፡

እንደ መላከታቦር መምህር ኢያሱ ገለፃ፤ አንድ አማኝ ፆም ለመፆም ሲያስብ በቅድሚያ ከጥላቻ እና ከቂም እራሱን አርቆ መሆን አለበት፡፡ ኃይማኖታዊ ስርዓቱን ጠብቆ አንድ ሰው መፆም ከቻለ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከት፣ ጤናን ብሎም ሰላምን እንዲያገኝ ያደርገዋል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሰባቱ አፅዋማት መካከል አብይ ፆም (ፆመ ሁዳዴ) አንዱ ነው፡፡ እድሜው ለመፆም የደረሰ ሁሉ እየፆመ፣ እየፀለየ፣ እያስቀደሰ በረከት የሚያገኝበት እንዲሁም ስለ ሀገራችን ሰላም፣ ፍቅር እና አንድነት እንዲሰፍን ለፈጣሪ የሚጠይቅበት ነው፡፡ የተቸገሩትም ሁሉ መልካም ነገር የሚያገኙበት ታላቅ በረከት ነው፡፡

ፆም ሲፆም ህዝበ ክርስቲያኑ ምሳሌ ሊያደርገው የሚገባው ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ከቆመ ሳይቀመጥ፤ ከዘረጋ ሳያጥፍ በገዳመ ቆሮንቶስ የተፈተነበት ነው፡፡ ከዚያም ፈተናውን አልፎ ለሰው ልጆች ሁሉ ተቃራኒ ሃሳብ የሚያመጣውን ሰይጣንን በፆም ድል የነሳበት መልካም ተምሳሌታችን ነው፡፡

በፆም ወቅት የሚታዩ ወይም የሚተገበሩ እሴቶች ፋይዳቸውን በተመለከተ መላከታቦር መምህር ኢያሱ ሲያስረዱ፤ ቅዱስ መጽሐፍ እንደተናገረው "ከወዴት እንደሆንክ አስብ" የሚለውን የት እንደሆንን የምናስብበት፣ ራሳችንን የምናይበት እንዲሁም ክርስትናችንንም ከምንጊዜውም በላይ ተግባራዊ የምናደርግበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን የመልካም እሴቶች ባለቤት መሆናችንን ተከትሎ ክፉዎች ሁሉ ደግ የሚሆኑበት፤ መጥፎ አስተሳሰብ ያላቸው መልካም ነገርን የሚያስቡበት ራሳቸውን የሚገዙበት ታላቅ ፆም ነው። በተለይ ደግሞ ምዕመኑ በአሁን ሰዓት የተቸገረን የሚረዳበት ጊዜ ነው፡፡

በተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) የሚገኙ ተማሪዎችም ቁርሳቸውን ለነዳያን የሚሰጡበት ከዚያም አልፎ ተርፎ አልባሳትንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ጭምር ይሰጣሉ። ይህን መሰሉ ተግባር አንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌትነትን የሚያሳይ ተግባር ነው፡፡ የተቸገረውን መርዳት፤ ለራበው በማብላት ለጠማው በማጠጣት ለታረዘው ደግሞ በማልበስ መልካምነት የሚንፀባረቅበት የፆም እሴቶቻችን ናቸውም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኡዝታዝ አቡበከር አህመድ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዝዳንቱ ልዩ አማካሪ በበኩላቸው እንዳስረዱት፤ "ፆም ከእስልምና መሠረታዊ ድንጋጌዎች ብሎም መመሪያዎች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ 'እናንተ ያመናችሁ ሁሉ ባለፉት ህዝቦች ላይ ፆም ግዴታ እንደተደረገው ሁሉ በእናንተም ላይ ተደረገ' ተብሎ በቅዱስ ቁርዓን ላይ ተገልፆአል፡፡ አማኝ የሆነ ሰው አቅሙ የሚችል ጤነኛ የሆነ ሰው መፆም ግዴታው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡"

በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የፆም እሴቶች የሆኑት እንደ አብሮነት፣ መተሳሰብ፣ አንዱ ለሌላው ማዘን፣ መልካም ስብዕና እና ርህራሄ ማሳየት፣እርስ በእርስ መደጋገፍ፤ ያለው ለሌለው የማካፈልና የመረዳዳት እሴት በረመዳን ወር ፍንትው ብሎ ይታያል፡፡ በተለይም ካለን ነገር ላይ ለሌላቸው የማካፈልና ፍቅራችንን ያለልዩነት በተግባር ማሳየት የቆዩ እሴቶቻችን ናቸውም" ሲሉ ኡዝታዝ አቡበከር ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባና አካባቢው ቀጠና ዋና ፀሐፊ መጋቢ በለጠ ኃጃሎ እንዳስረዱት ደግሞ፤ "በፆም ወቅት የሰው ልጅ ከመጥፎ ነገሮች የሚቆጠብበት ሃጥያትን የሚፀየፍበት ጊዜ ነው፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው ሃጥያትን ፈፅማ የምትፀየፍ ነፍስ እጅግ የተባረከች እንደሆነች ተገልጿል፡፡ በተለይ ወጣቱ እራሱን በዘመን አመጣሽ ግርግር ሳይዋጥ ከተለያዩ ነገሮች በመቆጠብ መልካም ሥነ ምግባርን ይላበሳል፡፡ መልካም ስብዕናን የያዘ ወጣት ለቤተሰቦቹ፣ ለቅርብ ወዳጆቹ እንዲሁም ለሀገር ትልቅ በረከት ነው። ቀጣይ ለሚመጣው ትውልድም ጥሩ ምሳሌ መሆን ይችላልም ብለዋል፡፡

በፆም ወቅት ያሉ እሴቶች ፋይዳቸውን በተመለከተ መጋቢ በለጠ እንደገለፁት፤ እርስ በእርስ ይቅር የመባባያ ጊዜ ነው፡፡ የተጣሉ የሚታረቁበት ሰላማዊ መንፈስ የሚነግስበት የፆም ወቅት ነው፡፡ "ቂም ይዞ ፀሎት ሳል ይዞ ስርቆት" አይቻልምና ሰዎች ከጥላቻ ወደ መግባባት ወደ እርቅ ወደ አንድነት የምንመጣበት የተባረከ የፆም ወቅት ጭምር ነው። አንድ ምዕመን በፆም ወቅት መቆጠብ ያለበት ከእህል ብቻ ሳይሆን አይኑ፣ አፉ፣ ጆሮው እንዲሁም መላ ህዋሳቶቹ ጭምር እንዲፆሙ ያዛል፡፡ አፍ መጥፎ ነገር ከመናገር አይንም የማይገባ ነገር ከማየት እግርም ወደ አልተገባ ስፍራ ከመሄድ የተከለከለ እንዲሆን በተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶች አማካኝነት ይነገራል፡፡ ይቅር መባባል አንዱ ከፆም የምናገኘው እሴት መሆኑን ተከትሎ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠረን ፍጡር መውደድ ያለንን ፍቅር ማሳየት ይቅር ማለት አንዱ አምላካችንን ስለመውደዳችን የሚያሳየን አስተምሮ ነውም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኡዝታዝ አቡበከር አክለውም፤ በፆም ወቅት የሚገኙ እሴቶችን ስናይ እንደ ግለሰብ ብሎም እንደ ሀገር ፋይዳው እጅግ የላቀ ያደርገዋል፡፡ ከምንም በላይ ግን የሰው ልጅ ፆም እንዲፈፅም የታዘዘውን መከወኑ መለኮታዊ መመሪያን ተግባራዊ ማድረግ እና ለፈጣሪ ታዛዥነቱን ነው የሚያሳየው፡፡ የሰው ልጅ በፍቃደኛነት በራሱ ላይ ገደብ ይጥላል ወይንም እቀባ ያደርጋል፡፡ ፈጣሪ ከከለከለው ነገር እራሱን በመከልከል በመተው በሌላ ጊዜ የተፈቀዱ እና መልካም የሆኑ ነገሮችን ከሚበላው ብሎም ከሚጠጣው ለፈጣሪ ክብር ሲል በተወሰነ ገደብ ውስጥ ያሳልፋል፡፡ ከብዙ ነገራቶች ራሱን ይገድባል፡፡ ይህም ታዛዥነት ወደ መንፈሳዊ ልዕልና ለመሸጋገር መንፈሳዊ ማንነቱን ለማጠናከር መሠረታዊ ነገር ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡

በመፆም ውስጥ የሚገኙ እሴቶችን አንድ በአንድ መከወን መቻል የሰው ልጅ በሥነ ምግባር ከፍታ ውስጥ እንዲኖር ያስችለዋል፡፡ ፆመኛ የሆነ ሰው አካሉ ሲደክም መንፈሱ እያደገ እየጎለበተ ይመጣል፡፡ ለፈጣሪ ታዛዥ እየሆነ በመጣ ቁጥር ሥነ ምግባሩም መልካም ይሆናል። ይህ ደግሞ የፆሙ ዋነኛ ዓላማ ሥነ ምግባርን ማስተካከል ነው፡፡ ፆመኛ የሆነ ሰው መጥፎ ንግግርን አይናገር፣ መጥፎ ተግባራትን አይፈፅም ሰው እንኳን ቢሰድበው ብሎም ሊገድለው ቢመጣ እንኳን ፆመኛ ስለሆነ ምንም አይናገርም፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ የረመዳን ፆምን በሚፆምበት ወቅት የ11 ወሩን ስንቅ የሚይዝበት የለውጥ ስንቁን የሚያገኝበት ነውም ብለዋል፡፡

በአፅዋማት ወቅት የሚታዩ መንፈሳዊ እና ማህበራዊ እሴቶች ከኃይማኖታዊ ይዘታቸው ባሻገር ለሀገር ግንባታ፣ ለኢኮኖሚ ብልጽግና እና ለህዝብ አንድነት ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ የሚናገሩት ደግሞ መጋቢ በለጠ ናቸው፡፡ እነዚህን እሴቶች ለሀገር በሚበጅ መልኩ ለማጠንከር ይቻል ዘንድ ራስን መግዛት፣ ለተቸገረ መራራት፣ ይቅር ባይነት እና ታማኝነት በኃይማኖት የታነጸ ዜጋ መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ እሴቶች ከቤተ እምነቶች ቅጥር ግቢ አልፈው በስራ ቦታዎች፣ በገበያ ስፍራዎችና በፖለቲካዊ መድረኮች ላይ ተግባራዊ አድርጎ ማስቀጠል በዋናነት የሀገርን ሰላምና ብልጽግና በእጅጉ እንዲረጋገጥ የሚያግዝ ተግባር ነውም ብለዋል፡፡

"በአጿማት ወቅት ተግባራዊ የሚደረጉ እሴቶችን ለሀገር በሚበጅ መልኩ እንዴት ማጠንከር ይቻላል?" ተብለው ለተጠየቀው ጥያቄ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ ዘሪሁን ዶዳ (ዶ/ር) ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ሀገራችን ኢትዮጵያ በብዝሃ ማንነት ደምቃ ለዘመናት የሕዝቦችን አብሮነት በማስጠበቅ ረገድ ኃይማኖታዊ ብሎም ማህበራዊ እሴቶቿን አጠናክራ ማስቀጠል በመቻሏ ምክንያት ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡ በተለያየ እምነት ውስጥ የሚገኙ አማኞችም ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎቻቸው በሚደግፈው አግባብ በሙሉ ስርዓቶችን እየፈፀሙ ይገኛሉ፡፡ ወቅቱ የፆም መሆኑን ተከትሎም የሰው ልጆች እራሳቸውን የሚገዙበት የትኛው መልካም ተግባር ነው፡፡ የትኛውስ ነው ከፈጣሪ ጋር የሚያስታርቀኝ በሚል ወደ እራሱ መለስ ብሎ የሚጠይቅበት ወቅት ስለመሆኑ ገልፀዋል፡፡

እንደ ዘሪሁን (ዶ/ር) ገለፃ፤ በአፅዋማት ወቅት ተግባራዊ የሚደረጉ እሴቶችን ለሀገር በሚበጅ አግባብ ለመጠቀም ያስችል ዘንድ እንደሚከተለው ፋይዳውን ጠቅሰዋል፡፡ አንድ አማኝ ፆም በሚፆምበት ወቅት የሚከውናቸው በጎ ተግባራት እንደ መረዳዳት፣ አንዱ ለአንዱ ማዘን፣ ያለውን መካፈል፣ ፍቅር፣ ርህራሄ እና መሰል ነገሮችን ዘወትራዊ በማድረግ ሂደቱን ማፅናት ያስፈልጋል የሚል እምነት አላቸው፡፡ በተለይም በፆም ወቅት በብዛት የሚነበቡ መንፈሳዊ ትምህርቶችን የዕለት ተዕለት ተግባር በማድረግ ምንጊዜም መልካምነትን እና በጎነትን በመሻት ፈጣሪ በሚፈልገው አግባብ መመራት መቻል ያስፈልጋል የሚል ሐሳብ አላቸው፡፡

በጾም ወቅት የሚደረጉ የምጽዋት እና የቸርነት ተግባራት በሀገር ደረጃ የሚያስገኙት ውጤት እጅግ ትልቅ ነው። መረዳዳትና መደጋገፍን ከማስፋፋት አንጻርም የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት የሚደረጉ ጥረቶች በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይቀሩ፣ በተደራጀ መልኩ የደካሞችን ኑሮ የሚደግፉ የልማት ሥራዎች ላይ እንዲውሉ ማስቻያ መንገድ ጭምር ነው፡፡ ያለው ለሌለው መስጠት የሚችል ከሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ የኢኮኖሚ ልዩነትን የሚያጠብ ሥነ-ልቦና ይፈጥራል። ከዚህ ባሻገርም አብዛኛው የጾም ወቅት የይቅርታና የፍቅር ጊዜ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህን ለሀገር ሰላም እጅግ አበርክቶው የላቀ ያደርገዋል፡፡ የውይይት ባህልን በማዳበር ቅሬታዎችን በጠረጴዛ ዙሪያ የመፍታት እና ይቅር ባይነትን የማስቀደም ልምድ ለሀገራዊ መግባባት ትልቅ መሠረት አለውም ሲሉ ተናግረዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የምርጫ ምንነት፣ መርሆች እና ዓይነቶች

## ክፍል አንድ

**ናደው ወርቁ (ዐቃቤ ህግ)**



### 1.1. የምርጫ ምንነት

ምርጫ ማለት የመንግስት ስልጣን ለመያዝ በድምጽ ብልጫ የሚወሰንበት ወይም የሚመረጥበት ወይም አንድ ሰው የተሻለ ነው ብሎ የሚያምንበትን አማራጭ ወይም ሐሳብ በምርጫ ካርድ፣ እጅ በማውጣት ወይም ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ሌላ ዘዴ የመግለጽ ሁኔታ ነው በማለት ዐውደ ጥበባዊ የሕግ መዝገበ ቃላት ትርጉም ይሰጠዋል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 2(5) ምርጫ ማለት በፌደራልና በክልል ሕገ መንግሥታት እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያ ወይም የድጋሚ ምርጫ ነው በማለት ትርጉም ይሰጣል፡፡ በአጭሩ ምርጫ ማለት አንድ ወይም ብዙ ሰዎች በተወሰኑ አካላት ውስጥ አስፈጻሚ ወይም ተወካይ ሆነው የሚመረጡበት አሰራር ነው ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡

### 1.2. የምርጫ መርሆች

የምርጫ መርህ ማለት እያንዳንዱ ምርጫ ሊያሟላው የሚገባው ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ አምስት ስር የሚከተሉትን መርሆች ያስቀምጣል፡፡

**1. ሁሉን አቀፍ ምርጫ፡-** ሁሉን አቀፍ ምርጫ ማለት ማንኛውም እድሜው ለምርጫ የደረሰ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በምርጫው እንዲሳተፍ ማስቻል ነው፡፡

**2. የእኩልነት መርህ፡-** ማንኛውም ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት ማንኛውም እድሜው ለምርጫ የደረሰና የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በሕግ ያልተገደበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በብሔር፣ በቋንቋ እንዲሁም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት እኩል የመምረጥ እና የመመረጥ መብት አለው፡፡ በኢፌደሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 38(1)(ለ) መሰረት አንድ ሰው ለመምረጥ እድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ማንኛውም ዜጋ እንዲመርጥም ሆነ እንዲመረጥ ማስገደድ አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእኩልነት መርህ መሰረት እያንዳንዱ መራጭ የሚሰጠው ድምጽ እኩል ነው፡፡

### 1.3. የምርጫ ዓይነቶች

በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 6 መሠረት አምስት የምርጫ ዓይነቶች አሉ። እነርሱም፡- ጠቅላላ ምርጫ፣ የአካባቢ ምርጫ፣ ማሟያ ምርጫ፣ ድጋሚ ምርጫ እና ሕዝበ ውሳኔ ናቸው፡፡

#### 1. ጠቅላላ ምርጫ፡-

ይህ ምርጫ የሕዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤት አባላቶች የሚመረጡበት ምርጫ ነው፡፡ (አዋጅ ቁጥር 1162/2011አንቀጽ 2(5)) በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 7 መሠረት ይህ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚደረግ ሲሆን በመርህ ደረጃ በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን በልዩ ሁኔታ ምርጫ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና ጉዳዩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሲያገኝ በተለያየ ጊዜ ሊደረግ ይችላል፡፡

በጠቅላላ ምርጫ ወቅት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአንድ የምርጫ ክልል አንድ ተወካይ ብቻ ይመረጣል፡፡ የምርጫ ክልል ማለት ለምርጫ አፈጻጸም እንዲያመች እና ሕዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በሕግ መሰረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፡፡ (አዋጅ ቁጥር 1162/2011አንቀጽ 2(15)) ለክልል ምክር ቤቶች አባላት ቁጥር በየክልሉ ሕግ መሠረት የሚወሰን ሲሆን፤ በአንድ የምርጫ ክልል ከአንድ ተወካይ በላይ ለክልል ምክር ቤቶች አባልነት ሊመረጥ ይችላል፡፡ይሁን እንጂ ክልሎች የምክር ቤቶቻቸውን አባላት ቁጥር ለመቀየር የሚሰጡት ውሳኔ ከእጩዎች የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ስድስት ወር አስቀድሞ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ይህ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ክልሎች የምክር ቤቶቻቸውን አባላት ቁጥር መቀየር አይችሉም፡፡

#### 2. የአካባቢ ምርጫ፡-

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 8 መሠረት ይህ ምርጫ በየደረጃው የሚካሄድ የብሔረሰብ ዞን፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ነው፡፡ በየደረጃው ለምክር ቤቶቹ የሚመረጡት ተወካዮች ቁጥር እያንዳንዱ ክልል በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡ ነገር ግን በክልሎች የሚወጡ እነዚህ ሕጎች ከህገ መንግስቱ እና ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡

#### 3. የማሟያ ምርጫ፡-

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 9 መሠረት ይህ ምርጫ የሚደረገው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው እና የመጀመሪያው በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች በተለያየ ምክንያት የጎደሉባቸው አባላት እንዲሟሉላቸው ለቦርዱ ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው፡፡ ሁለተኛው የይውረድልን ጥያቄ ሲቀርብ ነው፡፡ ይህ ማለት ስልጣን ላይ ያለው አካል በመረጠው ሕዝብ ጥያቄ አማካኝነት ከስልጣን እንዲወርድ ሲጠየቅ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ቦርዱ ጥያቄው በደረሰው ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማሟያ ምርጫ ያካሂዳል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ምክር ቤት የስራ ዘመኑ ሊጠናቀቅ የቀረው ጊዜ ስድስት ወር እና ከዚያ በታች ከሆነ የማሟያ ምርጫ አይካሄድም፡፡

#### 4. ድጋሜ ምርጫ፡-

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10 መሠረት ይህ ምርጫ ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ በአንዱ ምክንያት ሊካሄድ ይችላል፡፡

- ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ እና ድጋሜ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረበለት አቤቱታ ላይ ተመስርቶ የምርጫ መደገም ውጤትን የሚያስከትል ውሳኔ ሲወስን፤
- እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት ያልተቻለ እንደሆነ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10(2) መሠረት ድጋሜ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት ልብ ሊባሉ የሚገቡ ሶስት ነገሮች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

ሌላ አዲስ የመራጮች ምዝገባ ሳይካሄድ በምርጫ ክልሉ ወይም ችግሩ በተከሰተባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ተመዝግበው በነበሩ መራጮች እንደገና ይካሄዳል፡፡

ድጋሜ ምርጫ እንዲካሄድ ያስፈለገው ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ እና ድጋሜ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረበለት አቤቱታ ላይ ተመስርቶ የምርጫ መደገም ውጤትን የሚያስከትል ውሳኔ ከሆነ አዲስ የእጩዎች ምዝገባ ማካሄድ ሳያስፈልግ ቀድሞ በተመዘገቡ እጮዎች መካከል ብቻ ምርጫ ይደረጋል።

ለድጋሜ ምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ አይቻልም፡፡

#### 5. ሕዝበ ውሳኔ፡-

ይህ ምርጫ በአንድ የውሳኔ ሐሳብ፣ ሕግ ወይም የፖለቲካ ጉዳይ የአንድ ሀገር ሕዝብ ጠቅላላ ወይም በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሕዝቦች በቀጥታ ድምጽ የሚሰጡበት ምርጫ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 2(10) መሰረት ሕዝበ ውሳኔ ማለት የሕዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም የሕዝብ ውሳኔ ለማወቅ የሚደረግ የድምጽ አሰጣጥ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ምርጫ በኢፌደሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 47(3) መሠረት የክልል ምስረታ ጥያቄ ሲቀርብ ወይም በአንቀጽ 39(4) መሠረት የመገንጠል ጥያቄ ሲቀርብ ሊካሄድ ይችላል፡፡

አንባቢዎቻችን ክፍል ሁለትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን፡፡

## የቅጥር ማስታወቂያ

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ  አመልካቾችን አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ለህትመትና ዲጂታል ሚዲያ  ዘርፍ** | | | | | | | | |
| 1 | የዲጂታል ሚዲያ አዘጋጅና አቅራቢ | በማንኛውም የትምህርት ዝግጅትና ደረጃ ሆኖ የዲጂታል ፅንሰ ሀሳብ ላይ ልዩ ችሎታ እና ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች | የዲጂታል ፅንሰ ሀሳብ ክህሎት እና እውቀት ያለው<br>እንዲሁም ሞዴል አርትስቶች ጭምር መሳተፍ ይችላሉ | ሰፊ እና ጥልቅ ሀሳብን በአጭሩ እና ፈጠራ ባለው መልኩ የመግለፅ ክህሎት ያለው<br>የዲጂታል ፅንሰ ሀሳብ ክህሎት እና እውቀት ያለው<br>ከፍተኛ የሆነ የፈጠራ ክህሎት እና ለስክሪን ተስማሚ የሆነ ተክለ ቁመና እና ድምፅ ያለው<br>የዩቲዩብ ቲክቶክ ኢንስታግራም እና መሰል የማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ ይዘትን በማምረት እና በማሰራጨት ልምድ ያለው | እንደ አስፈላጊነቱ | በ ታ ለ ን ት ግዢ | በ ተ ቋ ሙ አሰራር እና ስምምነት | አ/አ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት  ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. አርቲስቶች እና ሞዴሎች እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ እውቅና ያላቸው ባለሙያዎች ይበረታታሉ
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. የዩቲዩብ ቲክቶክ ኢንስታግራም እና መሰል የማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ ይዘትን በማምረት እና በማሰራጨት ልምድ ያለው
5. የምዝገባው ቀን ከመጋቢት 07 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ መጋቢት 18 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

## አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090901863 በወ/ሮ ሽቱ ሙዘሚል ጁሀር ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 30/06/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በእነ ጠጅቱ ካሳዬ ጣሰው እና እነ በቀለች ተመስገን ደንበባ (6 ወራሾች) ስም በልደታ ክ/ማ የቀድሞ ወረዳ 03 የቀድሞ ቀበሌ 43 የቤት ቁጥር 814 በቀን 24/02/2004 የካርታ ቁጥር ል.09/30/1900/00 ሴሪ ቁጥር 005084 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ሙብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010  አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በእነ ሚሊዮን ተፈራ ሳህሌ (7 ሰዎች) በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 08 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070803714/3704 በሴሪ ቁጥር 0170858 በእነ ሚሊዮን ተፈራ ሳህሌ (7 ሰዎች) ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የወ/ሮ ትጎደድ አባተ አለምነህ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 በአሁኑ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የሆነው የመለያ ኮድ ቁጥር AA000051207334281O2023 ሴሪ ቁጥር C 169246 በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቸዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት/ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ኤፍሬም ገዛኸኝ ጋረደው የተባለው ግለሰብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 05 የሚገኘው የይዞታ ካርታ ቁጥር 07/91/2481/7894/800333/802416/03 በሴሪ ቁጥሩ 0245237 የሆነ ኤፍሬም ገዛኸኝ ጋረደው ስም ያለ የይዞታ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በሚኪያስ ፍቅሬ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ03/12/2/14272/0363/14/02 የተሰጠበት ቀን 24/08/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት 250 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በሚኪያስ ፍቅሬ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ03/12/2/14272/0363/14/02 የተሰጠበት ቀን 24/08/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት 250 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ የይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያለን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 08 በአዲሱ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 079 በአቶ ተፈራ ሥርፀ ድንግል እና በተጋሪመ ወ/ሮ እንግዳወርቅ በየነ ስም የወጣው ቁጥሩ አ/13/54/2731/00/00 ሴሪ ቁጥር 000111 በቀን 19/04/2004 ዓ.ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 02/07/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል  ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ

# የኮሌጁ የተወዳዳሪነት አቅም

- **ከመጋቢት 3 ቀን 2018 ዓ.ም የጀመረው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት እስከ መጋቢት 7 ቀን 2018 ዓ.ም ይቆያል**
- **ኮሌጁ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመርሃ ግብሩ ላይ አቅርቧል**

**በሄለን ጥላሁን**

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በአዲስ አበባ ብሎም በኢትዮጵያ የትምህርት ታሪክ ውስጥ በእድሜ አንጋፋ እና የብዙ ዓመታት የማሰልጠን ልምድ ካላቸው የትምህርት ተቋማት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ ኮሌጁ ዛሬ ያለበት ደረጃ ለመድረስ በየዘመናቱ በርካታ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ በሚያሠለጥናቸው ሠልጣኞች ብዛት፣ በሥልጠና ዘርፎች፣ በተቋማዊ አደረጃጀት፣ በሠው ኃይል እና በግብዓት አቅሙን በማሳደግ አሁን ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም እንደ ሀገር ወሳኝ የሆነውን የተማረ የሰው ሃይል በተለይም በሙያዊ ክህሎት የበቁ ሙያተኞችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት አይተኬ ሚናውን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ዲን አቶ ወንድም ሲያምረኝ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፣ በምርት ጥራት ላይ የተመሰረተ ተወዳዳሪ ባለሙያዎችን በማፍራት ሀገራዊ ሃላፊነቱን ለመወጣት ያስችል ዘንድ በንድፈ ሃሳብ ብሎም በተግባር ተፈትኖ ብቃቱ የተረጋገጠ የሠው ኃይል ለማፍራት ኮሌጁ በተጠናከረ መልኩ እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ የሚያሰለጥናቸውን ሙያተኞች፣ በተለያየ ዘርፍ በአሰልጣኝነት የተሰማሩ አሰልጣኞች እንዲሁም የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁን አጠቃላይ ተቋማዊ ብቃት ለማወቅ፣ ከሌሎች ልምድ ለመማር፣ የበለጠ እንዲሻሻል ለማድረግ የተለያዩ አጋጣሚዎችን ይጠቀማል። ከእነዚህ መካከል በከተማ አስተዳደር እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ሳምንት መርሃ ግብሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ዘንድሮ በአዲስ አበባ ደረጃ በሚካሄደው 16ኛው ከተማ አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ለመሳተፍ ዝግጅቱን አጠናቅቋል፡፡

ተጠባቂው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት በተለያዩ መርሃ ግብሮች እንደሚካሄድ የሚናገሩት የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ምክትል ዲን፣ ኮሌጁ በመርሃ ግብሩ በተለያዩ ዘርፎች ተሳትፎውን እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በኢትዮጵያ የትምህርት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስም ያለው አንጋፋ ተቋም መሆኑ ያበረከተለትን ዕድል በመጠቀም መድረኩን በአግባቡ ለመጠቀም ዝግጅት አድርጓልም ብለዋል።

ምክትል ዲኑ አክለውም፤ የቴክኒክና ሙያ ሳምንት መካሄዱ በዋናነት የሰልጣኞችን የፈጠራ ስራ ማሳየትና




ፎቶ- ከገጸ ድር
ኮሌጁ በቴክኒክና ሙያ ሳምንት ለዕይታ ካቀረባቸው ስራዎች በጥቂቱ

የዘርፉን አስፈላጊነት ለማስተዋወቅ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት፣ የፈጠራ ስራዎችን ለማበረታታት እና የዘርፉን አስፈላጊነት ለማብሰር የሚካሄድ ትልቅ መድረክ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ ያሉ ተማሪዎች፣ አሰልጣኞች እና የኢንዱስትሪ ባለቤቶች የሚገናኙበት ትልቅ አገናኝ ድልድይ እንደሚሆን ጭምር አስታውቀዋል፡፡

ልክ እንደ ሌሎቹ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ሁሉ የሰልጣኞችን የተግባር ተኮር ክህሎት ለማሳደግ ይቻል ዘንድ በንድፈ ሃሳብ ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር የተደገፈ እውቀት በመስጠት የሰልጣኞችን አቅም ማሳደግ ላይ ያተኩራል፡፡ ሰልጣኞችም ስልጠናቸውን እንዳጠናቀቁ በቀጥታ ወደ ስራ እንዲገቡ በማስቻል ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለሀገር እድገት ቁልፍ የሆኑና ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውን ብቁ ባለሙያዎች በማቅረብ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት ለማሟላት በሚደረገው ጥረት ኮሌጁ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት፣ በመምረጥ፣ በመቅዳትና በመፈተን የማምረት አቅምን ለማሳደግ በሚያስችል አግባብ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እነዚህንና መሰል ስራዎችን በመስራት ሂደት እንደ ቴክኒክና ሙያ ሳምንት መርሃ ግብሮች መካሄዳቸው ትልቅ መነቃቃትን ፈጥረዋል፡፡ የመርሃ ግብሩ አስፈላጊነት በተመለከተ አቶ ወንድም ሲያምረኝ ሲያስረዱ፣ "የፈጠራ ስራዎች በኤግዚቢሽን ለእይታ ይቀርባሉ። በቴክኒክና ሙያ ሳምንት ሰልጣኞች የሰሯቸውን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ ማሽኖች እና የፈጠራ ውጤቶች ለህዝብ እይታ ይቀርባሉ። ይህም ሰልጣኞች ያላቸውን ክህሎት ለገበያ እንዲያስተዋውቁ እድል ይፈጥራል" ብለዋል፡፡

በመርሃ ግብሩ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል፡- የልምድ ልውውጥ እና ለተቋማቱ ዕድገት እና መሻሻል የሚያግዙ ውይይቶች እንደሚገኙበት አቶ ወንድም ሲያምረኝ ጠቁመዋል። በመርሃ ግብሩ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ የፓናል ውይይቶች እንደሚካሄዱ በማንሳት፣ እንዲህ ዓይነት ውይይቶች በቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና በኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ትስስር ከፍ እንዲል ያግዛል፡፡ ስልጠናዎቻቸውን አጠናቅቀው የጨረሱ ሰልጣኞች ከወሰዷቸው የሥልጠና መስኮች ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው በተለይም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰው ሃይል በማቅረብ ረገድ ሰፊ እድል ይፈጥራል። በሚደረጉ የልምድ ልውውጦችና ውይይቶች የስራ አጥነትን ለመቀነስ የሚረዱ አዳዲስ ስልቶች ይቀየሳሉ፡፡ በተለይም የገበያ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎች ላይ ምክክር እንደሚደረግ አስታውቀዋል፡፡

ምክትል ዲኑ በማብራሪያቸው፤ የክህሎት ውድድር ማድረግ በመርሃ ግብሩ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ይካተታል፡፡ በግንባታ፣ በኤሌክትሪክ፣ በልብስ ስፌት፣ በእንጨት ስራ እና መሰል የስልጠና መስኮች ላይ እርስ በእርሳቸው የክህሎት ውድድር በማድረግ ብቃታቸውን የሚያሳዩበት መድረክ ጭምርም ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እንደሚሆን አስታውቀዋል፡፡ ይህ ሲባልም ቴክኒክና ሙያ ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት ያለው ፋይዳ ተንትኖ በማስቀመጥ ወጣቶች ወደ ሙያ ተቋማት እንዲገቡ ቅስቀሳ ለማድረግ ምቹ የሆነ መድረክ ነው። በተለይም "በውጤት ደከም ያሉ ሰልጣኞች የሚሰለጥኑት ስልጠና ነው" የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት በማረቅ ረገድ በቴክኒክና ሙያ ሳምንት የሚቀርቡ ስራዎች አፍ አውጥቶ የሚመሰክሩበት መድረክ ነው"ብለዋል፡፡

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በቴክኒክና ሙያ ሳምንት ላይ ከመሳተፍ ባሻገር ለየት ባሉ ስራዎች ወደ መርሃ ግብሩ እንደሚመጣ የሚናገሩት ምክትል ዲኑ፣ በኤስቴቲክስ የትምህርት ክፍል አማካኝነት የሚቀርቡ የስዕል፣ የቅርፃ ቅርፅ አውደ ርዕዮች እንዲሁም የሙዚቃ እና የቴአትር ስራዎች ይቀርባሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉ መርሃ ግብሮች መዘጋጀት መቻላቸው፤ ሰልጣኞች ብሎም አሰልጣኞች ያላቸውን እምቅ አቅም እንዲያወጡ ከማድረግ ባሻገር ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር ያስችላልም ብለዋል፡፡

በሌሎች የስልጠና መስኮች ላይ የሚሳተፈው ኮሌጁ በፋሽንና ዲዛይን፣ በኮንስትራክሽን፣ በኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ፣ በእንጨት ስራ እንዲሁም በሌሎችም ዘርፎች ላይ አሉኝ የሚላቸውን ስራዎች እንደሚያቀርብ ምክትል ዲኑ አስታውቋል፡፡ በአሰልጣኞች ብሎም በሰልጣኞች የተሰሩ የፈጠራ ስራዎች ችግር ፈቺና እጅ ከምን ለሚለው ጥያቄ ጥሩ ምላሽ የሚሰጡ ስራዎችን ይዘው እንደሚቀርቡም አስታውቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የትምህርት ታሪክ ተፈሪ መኮንን የትምህርት ተቋም በተለያዩ ጊዜያት ስያሜውን እየቀየረ አሁን ላይ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ላይ ደርሷል። እድሜውን የሚመጥን ውጤታማ ስራዎችን ከመስራት አንፃርም እስካሁን እየተዘጋጁ ባሉ የቴክኒክና ሙያ ሳምንታት ላይ ግንባር ቀደምትነቱን በውጤት ለማስመዝገብ ችሏል፡፡ በ2017 ዓ.ም በተካሄደው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ላይ በኤስቴቲክስ እንዲሁም በፋሽን ዲዛይን የትምህርት መስኮች የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ስለመቻሉ ምክትል ዲኑ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ለተመዘገቡ ውጤቶች ኮሌጁ የተግባር ላይ ልምምድ ስራውን በትኩረት መስራቱ፣ አሰልጣኞች ብሎም ሰልጣኞች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣቱ፣ የተለያዩ የስልጠና ዘርፎችን አመራሩ ለመደገፍ የሄደበት አግባብ እጅግ መልካም መሆኑ እንዲሁም ስራዎችን በሚፈለገው ጥራትና ፍጥነት ለመከወን በግቢው ማህበረሰብ ዘንድ ያለው መስተጋብር እጅግ ወሳኝ የሆነ ሚናን እንደተጫወተ ገልፀዋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ሳምንት መጋቢት 3 እስከ መጋቢት 7 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ይካሄዳል። በአሰልጣኝ፣ በኢንተርፕራይዞች እንዲሁም በሰልጣኞች የተሠሩ የፈጠራ ስራዎች ለእይታ ይቀርባሉ፡፡

# ኪነ ጥበባዊ ድግሶች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል፣ የስዕል አውደ ርዕይና የመጽሐፍት ምረቃ ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል

17ኛው ከተማ አቀፍ የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል ሳምንት ከዛሬ ጀምሮ እስከ መጋቢት 7 ቀን 2018 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ይካሄዳል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ በየዓመቱ የሚያሰናዳው ይህ ፌስቲቫል ዘንድሮ "የጥበብ ስጦታ ለኢትዮጵያ ከፍታ!" በሚል መሪ ሃሳብ በመስቀል አደባባይ ይካሄዳል፡፡ ፌስቲቫሉ የከተማዋን የጥበብ መንፈስ የሚያድስ እንደሚሆንም ተገልጿል።

ላለፉት 16 ዓመታት በተከታታይ ሲካሄድ የቆየው ይህ ፌስቲቫል፣ በዚህ ዓመትም ለ17ኛ ጊዜ የሚካሄድ ነው። በመርሃ ግብሩ በ16 የተለያዩ የጥበብ ዘርፎች የሚካሄዱ ውድድሮች እንዲሁም የፈጠራ ሥራዎች የሚቀርቡበት በተለይም አውደ ርዕይ፣ ሲምፖዚየም (አውደ-ጥናት)፣ ጥበባዊ ውይይቶችና የልምድ ልውውጦች፣ ውድድሮች፣ ለዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የጥበብ ባለውለታዎች የሚዘከሩበት ልዩ መድረክ እና ሌሎችም እንደሚካሄዱበት ተገልጿል።

የፌስቲቫሉ ዋና ዋና ዓላማዎች በአዲስ አበባ ያሉ የኪነ-ጥበብ ተሰጥኦዎችን ለሕዝብ ማስተዋወቅ፣ በጀማሪ እና በባለሙያ (Professional) ጥበበኞች መካከል የልምድ ልውውጥ መፍጠር፣ አዳዲስ ባለተሰጥኦዎችን ማበረታታት፣ ዕውቅና መስጠት እና በኪነ-ጥበብ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ እንደሆነ ተገልጿል።

## መጽሐፍት

"አክሊሉ" የተሰኘው ታሪካዊ ልብ ወለድ መጽሐፍ በዛሬው ዕለት ይመረቃል፡፡ መጋቢት 5 የጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ልደታቸው ሲሆን፤ "አክሊሉ" የሚል በህይወት ታሪካቸው ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ መጽሐፍም በዕለቱ ይመረቃል፡፡ የመጻሐፉ ደራሲ ሰላማዊት ታደሰ (ዶ/ር) ስትሆን ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ጀምሮ በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት ዘጠነኛ ፎቅ እንደሚመረቅ ተገልጿል፡፡

## የሐሳብና የመጽሐፍት መድረክ

በዛሬው ዕለት የሐሳብ እና መጽሐፍት መድረክ ይካሄዳል፡፡ የውይይት ርዕሱ "የዓለም መቀዛቀዝ ለኢትዮጵያ ተስፋ? የአምራች ኢንዱስትሪው ዕውነታ፣ ዕድሎችና፣ አቅጣጫ..." የሚል ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ መነሻ ሐሳብ የሚያቀርቡት ብርሃኑ በሻህ (ዶ/ር) እና አማረ ማተቡ (ዶ/ር) ናቸው፡፡ ውይይቱ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ አራት ኪሎ ዋልያ አዳራሽ ኢክላስ ሕንጻ 4ኛ ፎቅ ይካሄዳል፡፡


## የስዕል አውደ ርዕይ

"የፈጠራ ጉዞን ማስተጋባት" የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል። አውደ ርዕዩ የተከፈተው ባሳለፍነው ሐሙስ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የሴት ሰዓሊያን ማህበር የ17 ሰዓሊያን ሥራዎች ያቀረበበት ነው፡፡ ፈንድቃ የባህል ማዕከል እና ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በመተባበር ያዘጋጁት ይህ አውደ ርዕይ 24 ሰዓት ለተመልካች ክፍት የሆነና እስከ መጋቢት 21 ቀን 2018 ዓ.ም የሚቆይ ነው፡፡

# የቁጥር ጨዋታ


## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር። የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል። የመጀመሪያው 9 × 2 + 5 = 23 ይሆናል፡፡ ሁለተኛውና ከታች የሚገኘው 6 × 3 + 4 = 22 ነው፡፡ ሁለተኛው 1 × 4 + 5 = 9 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥቄው መልስ 1 × 4 + 5 = 9 ነው፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **1** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ለዓለም የተረፈ ሀብት

- ፊቼ ጨምበላላ ከውበት ባሻገር በውስጡ በርካታ እሴቶች መያዙን መረጃዎች ያመላክታሉ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃጎ አገኘሁ





ፎቶ- ከገፀ ድር

የፊቼ ጨምበላላ ስርዓት በከፊል

**በጊዜው አማረ**

የሲዳማ የዘመን መለወጫ ተፈጥሮና ሰው በአንድ ድምፅ ለሰላም የሚዘምሩበት ረቂቅ ምስጢር ነው። ምክንያቱም ፊቼ ጨምበላላ በዓል ብቻ አይደለም፤ የነፍስ መታደሻ፣ የቂም መደምሰሻና የፍቅር መድረክ ነው። የጨረቃና የከዋክብት ውህደት የአዲሱን ዓመት ብርሃን ሲያበስሩ፣ የሰው ልጅ ልብም በይቅርታ ብርሃን ይሞላል።

በፊቼ ጨምበላላ ምድር ከጥላቻ ትላቀቃለች። ገንዘብ ያበደረ "ክፈለኝ" ብሎ ተበዳሪውን አይጠይቅም፡፡ አያስጨንቅም፡፡ ምክንያቱም በዚያች ዕለት ከገንዘብ ይልቅ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት ይገዝፋልና። የበደለ ካሳ ሳይጠየቅ፣ የገፋ ይቅርታ ሳይለምን፣ ሁሉም በነጻነት ወደ ፍቅር አደባባይ ይተምማሉ። ይህ እሴት የሲዳማ ሕዝብ ለሀገራችን እና ለዓለም የቸረው የሞራል ልዕልና ማሳያ ሲሆን፣ ሰላም በቃላት ሳይሆን በተግባር የሚተረጎምበት ሕያው ተምሳሌት ነው።

በፊቼ ጨምበላላ ዋዜማ፣ በሲዳማዎች ቤት ውስጥ የሚበራው መብራት የደስታ ብቻ ሳይሆን የጥበቃም ጭምር ነው። በዕለቱ ዛፍ አይቆረጥም፣ አዝመራ አይታጨድም፣ እንስሳትም አይታረድም። ተፈጥሮ ሙሉ ዕረፍት ታገኛለች። ትጠበቃለች፡፡ ይህ "ሕይወትን የማክበር" ጥበብ፣ በሰውና በፈጣሪ፣ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ጥብቅ ቁርኝት ያሳያል። በሲዳማዎች ምድር ቄጠላ ሲጨፈር፣ እግሮች ወደ ሰማይ ሲዘልሉ፣ ትከሻዎች በአንድነት ሲወዘወዙ፣ የሚሰማው የአንድነትና የፍቅር የልብ ትርታ ነው።

የባህል አጥኚው አቶ ብርሃኑ ሃንካራ በአንድ ወቅት በዓሉን አስመልክተው ለቢቢሲ እንደገለጹት "የፊቼ ጨምበላላ በዓል የሲዳማ ሕዝብ ማንነቱን ከተረዳበት ጊዜ አንስቶ ሲከበር የቆየ ነው" ይላሉ። ፊቼ ጨምበላላ በዓል የሚከበርበት ቋሚ ቀን የለውም። በአያንቱዎች ጥቆማ መሰረት በዓሉ የሚከበርበት ቀን ይቆረጣል። ከዚያም ለበዓሉ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ ይጀመራል። ከዋዜማው አንስቶ በዓሉ መከበር ይጀምራል። ጎረቤት ተሰብስቦ ከእንሰት የሚዘጋጀውን ቦርሻሜ ተብሎ የሚጠራውን ምግብ ይመገባሉ። ለበዓሉ ከሚበሉ ባህላዊ ምግቦችና ከሚከናወኑ ጭፈራዎች በተጨማሪ የተለያዩ ባህላዊ ሁነቶችም ይካሄዳሉ። ቄጠላ፣ ኛፋሮና የመሳሰሉ ሙዚቃዎችም በበዓሉ ይከወናሉ።

የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃጎ አገኘሁ በበኩላቸው የዘንድሮውን ፊቼ ጨምበላላ አስመልክተው በሰጡት መግለጫ በዓሉ ለሲዳማ ብሔር ከዘመን መለወጫነት ባሻገር ትልቅ ትርጉም ያለው የማንነቱ መገለጫ፤ የነፃነትና የፍቅር ማዕድ ሁሉም በጋራ የሚቋደስበት፤ የመንፃትና የመታደስ፤ አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበት፣ በዳኤ ቡሹ እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅር፣ አክብሮትና ደስታ የሚገልጹበት ነው ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በውስጡ ያሉ በርካታ እሴቶች በተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚገለጹበት፣ እርቅ የሚፈፀምበትና ሀዘን የሚያበቃበት አልፎ ተርፎም በዓሉ ሲከበር አብሮነትን፣ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ መረዳዳትን፣ መደማመጥን እንዲሁም መተባበርን የሚያጎሉ ድርጊቶች የሚፈጸሙበት ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

## ስለበዓሉ አከባበር በጥቂቱ

በቅድመ ፊቼ በዓሉ (ፊቼ) የሚውልበትን ቀን የመቁረጥ (ላላዋ)፣ ስለቀኑ ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር መምከር (ፋጆ)፣ በዓሉ የሚከበርበትን ቀን ሕዝብ በሚሰበሰቡበት ማወጅ (ላላዋ)፣ ጭሜሳዎች ስላላፈው ዓመት በሰውና በእንስሳ ስለተፈፀመ በደል ንስሃ እየገቡ የሚፆሙበት (ኡሱራ)፣ የፊቼ ቀን መቃረቡን ማብሰሪያ የጭሜሳዎች ቄጣላ (ሳፎተ ቄጣላ)፣ ወጣቶች ለበዓሉ የሚያስፈልጋቸውን ልብስና ቁሳቁስ ማሟላታቸውን እየገለፁ የሚከውኑት ቄጣላ (አድቻ ቄጣላ) እና ሁሉን አቀፍ ዕርቅ (አራራ) ይከናወናሉ፡፡

የፊቼ ዕለት ፊጣራ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በዕለቱ ከ9:00 ወይም 10:00 ሰዓት ገደማ ደጅ ላይ በአግድም በእርጥብ እንጨት መሿለኪያ (ሁሉቃ) ተሠርቶ ሰውና የቤት እንስሳት በዚያ የሚሾልኩበት፣ ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ የመሸጋገር ተምሳሌት ይከናወናል። ከ12:00 ሰዓት ጀምሮ ደግሞ ቡሪሳሜ በሻፌታ ተዘጋጅቶ በጋራ ይበላል። ቡሪሳሜ በጋራ የመቋደስ ሥርዓት መጀመሪያ በጎሳ መሪ ወይም ጭሜሳ ቤት ይሆንና እንደየ እድሜ ቅደም ተከተል በዙር ሁሉም ቤት ይደርሳል።

በማግስቱ ቀኑ ጨምባላላ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህ ለልጆች፣ ለከብቶች፣ ለዱር እንስሳትና ለተፈጥሮ ልዩ ቀን ነው። በጨምባላላ ዕለት ልጆች ከቤት ቤት እየዞሩ "አይዴ ጨምባላላ!" እያሉ እናቶች "ኢሌ ኢሌ" ብለው ቡሪሳሜ እያበሏቸው ቀኑን ሲቦርቁ ይውላሉ። ከብቶችም ጥሩ ግጦሽ ወዳለበት የሚሰማሩበት፣ በአርጩሜ የማይመቱበት ዕለት ነው። የዱር እንስሳት የማይታደኑበት፣ የዛፍ ቅርንጫፍ የማይቆረጥበት ዕለትም ነው፡፡

ዩኔስኮ በይፋዊ ገጹ ላይ ባሰፈረው ጽሑፍ ፊቼ ጨምበላላ ከበዓልነት ባለፈም የእውቀት ሽግግር የሚደረግበት እለት ነው ይላል፡፡ ተቋሙ እ.ኤ.አ. በ2015 "Fichee-Chambalaalla, New Year festival of the Sidama people" በሚል ርዕስ ባሰፈረው ጽሑፍ ወላጆች በበዓሉ ላይ ወጉንና ባህሉን ለልጆቻቸው በምርቃት፣ በጭፈራ እና በቃል ያስተላልፋሉ። በተለይም ሴቶች የፀጉር አሰራርን እንዲሁም የቡሪሳሜ አዘገጃጀት እውቀትንና ክህሎትን ለሴት ልጆቻቸውና በአካባቢያቸው ለሚገኙ ልጃገረዶች ያስተምራሉ በማለት ገልጾታል።

## ጨምበላላ እና ተዝናኖት

ፊቼ ጨምበላላ ቁምነገርና ተዝናኖት የሚሸመንበት እለት ነው፡፡ ከጨምባላላ ዕለት ቀጥሎ ሁሉም ጎሳ በየጉዱማሌው ስሜቱን በቄጣላ፣ በፋሮና ልጃገረዶች በሆሬ ክዋኔ ለሁለት ሳምታት የሚገልፁበት ጊዜ ይሆናል። የፊቼ ማሳረጊያ ዕለት ፊቺ ፋሎ ይባላል። በዚህ ዕለት ሁሉም ሰው ወደ ታላቁ ጉዱማሌ ይከትማል።

በፊቼ ጨምበላላ በዓል ማጠቃለያ ላይ የሚቀርበው ቄጠላ፣ የሲዳማ ሕዝብ ታሪኩን፣ እሴቱንና ወንድማማችነቱን የሚገልጽበት ደማቅ ባህላዊ የጭፈራ ሥነ-ሥርዓት ነው። ይህ ትዕይንት ወጣቶች፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች በአንድነት በመሆን የአዲሱን ዓመት መባቻ የሚያበስሩበትና የሕዝቡን አንድነት የሚያሳዩበት ልዩ የጭፈራና እና የተዝናኖት መድረክ ነው።

በዚህ ባህላዊ ሙዚቃና ጭፈራ ወቅት፣ አገርና ዘመን በክብር ይወደሳሉ። ባለፈው ዓመት የተከናወኑ መልካም ተግባራት እየተዘከሩ፣ አዲሱ ዘመን የሰላምና የብልጽግና እንዲሆን በዜማ ይማጸናሉ። በተለይም የአገር ሽማግሌዎች ላበረከቱት የላቀ አስተዋጽኦ፣ ለሰጡት ጥበብና ለጠበቁት ሰላም በግጥም የሚወደሱበት፣ ታዋቂ ግለሰቦችም ለሕዝብ በሰሩት በጎ ሥራ የሚመረቁበት የክብር መገለጫ ነው፡፡

ቄጠላ እንዲሁ ዝም ብሎ ጭፈራ ሳይሆን፣ የትውልድ ቅብብሎሽ የሚካሄድበት ታላቅ የባህል መድረክ ነው።፤ ተዝናኖት እና ቁም ነገርን በአንድ የያዘ፡፡ ተሳታፊዎቹ በዜማና በዝላይ የታጀበ እንቅስቃሴ እያደረጉ ወደ አደባባይ (ጉዱማሌ) በመትመም፣ የሲዳማን ሕዝብ ኩራትና ማንነት ለዓለም ያሳያሉ። ይህ ሥነ-ሥርዓት በዓሉ በታላቅ ድምቀት የሚጠናቀቅና በቀጣዩ ዓመትም በሰላም ለመገናኘት ቃል የሚገባበት የማኅበረሰቡ የጋራ ድምፅ ነው።

## ፊቼ ጨምበላላ የሀገርና የዓለም ሃብት

የፊቼ ጨምበላላ በዓል በዓለም አቀፉ የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) በማይዳሰሱ የዓለም ቅርሶች ዝርዝር ውስጥ መመዝገቡ፣ ለሲዳማ ሕዝብም ሆነ ለኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል። ይህ እውቅና በዓሉን ከሀገር ውስጥ ባህላዊ ክዋኔ ወደ ዓለም አቀፍ የሰው ልጅ የጋራ ሀብትነት አሸጋግሮታል።

ማንኛውም ቅርስ በዩኔስኮ ሲመዘገብ የዓለም የቱሪስት መዳረሻ የመሆን ዕድሉ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል። ፊቼ ጨምበላላም ለኢትዮጵያ፣ ለሀዋሳና ለሲዳማ ክልል ትልቅ የቱሪዝም በር ከፍቷል።

በየዓመቱ በዓሉ በሚከበርበት ወቅት ከውጭና ከሀገር ውስጥ የሚመጡ ቱሪስቶች ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል። ይህ ደግሞ ለሆቴሎች፣ ለትራንስፖርት ዘርፉና ለባህላዊ ምርቶች አቅራቢዎች ትልቅ ገቢ ያስገኛል። በተጨማሪም የባህል አልባሳትን የሚያመርቱ፣ ባህላዊ ምግቦችን የሚያቀርቡና የቱሪስት አስጎብኚዎች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

የቢሮ ኃላፊው አቶ ጃጎ አገኘሁ የዘንድሮን በዓል ፊቼ ጫምባላላ ከሲዳማ እሴትነት አልፎ በዩኔስኮ የሰው ልጆች ወካይ የማይዳሰስ ባሕላዊ ቅርስ ዝርዝር መዝገብ ላይ መስፈሩን ተከትሎ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች የሚታደሙት ልዩ በዓል መሆኑን የገለጹትም ይህንኑ የሚያመላክት ነው።

በተጨማሪም የፊቼ ጨምበላላ እሴት የሆኑት ይቅርታ፣ እርቅ፣ ተፈጥሮን መንከባከብና ፍቅር ለኢትዮጵያ የሰላም ግንባታ ሂደት ትልቅ ትምህርት የሚሰጡ ናቸው። ዩኔስኮ ይህን የመሰለ የሰላም እሴት ያለው በዓል መመዝገቡ፣ ኢትዮጵያ የሰላም እሴቶች መፍለቂያ መሆኗን ለዓለም ያሳያል።

ፊቼ ጨምበላላ ኢትዮጵያ በርካታ የዩኔስኮ ቅርሶች ያሏት ሀገር መሆኗን በማጠናከር፣ የሀገሪቱን ገጽታ በጥሩ ሁኔታ ለመገንባት (Nation Branding) ይረዳል። ይህም ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ መድረክ ያላትን ተሰሚነትና ክብር ይጨምራል።

በአጠቃላይ፣ የፊቼ ጨምበላላ በዩኔስኮ መመዝገብ የሲዳማን ሕዝብ ማንነትና ባህል ለዓለም ከማስተዋወቁም በላይ፣ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የዲፕሎማሲ ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ይህ ቅርስ ተጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ ደግሞ መንግሥትና ሕዝቡን ጨምሮ የባለድርሻ አካላት የጋራ ኃላፊነት ነው።

ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# አካዳሚው ለ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስኬታማነት በምን ልክ ያግዛል?

- **የአመራር አካዳሚዎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለጥናት፣ ምርምርና ማማከር አገልግሎት ማዋላቸው ለተቋማዊ ብቃት ዕድገት ወሳኝ ሞተር መሆኑ ተመላክቷል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**


በፈጣን ለውጥ ውስጥ ባለችው የዛሬዋ ዓለም፣ የመንግስትና የግል ተቋማት ስኬት የሚወሰነው በቴክኖሎጂ የታገዙ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ባላቸው መሪዎች ነው። እንዲህ ያለውን ብቁ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ደግሞ የአመራር አካዳሚዎች ብቁ አስተዋፅኦ አላቸው፤ አካዳሚዎች የዲጂታል መሠረተ-ልማቶችን በመጠቀም የተቋማትን የአሠራር ክፍተት የሚደፍኑ የልቀት ማዕከላት ሆነዋል።

አመራር አካዳሚዎች የአመራሩን የክህሎት ክፍተት በመለየት ላይ የተመሰረተ ስልጠና ከመስጠት ባለፈ፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምርን ከተግባራዊ የማማከር አገልግሎት ጋር በማጣመር የተቋማትን ምርታማነት እያሳደጉ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው የሲንጋፖር ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ (CSC) አብነት የሚሆን ተሞክሮ እንዳለው መረጃዎች ያመላክታሉ።

የሲንጋፖር ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ (CSC) የሀገሪቱን የመንግስት ሰራተኞችና የግል ዘርፍ መሪዎችን በቴክኖሎጂ የታገዘ ቀጣይነት ያለው ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ፣ ሲንጋፖር ቀልጣፋና ከሙስና የጸዳ ቢሮክራሲ እንዲኖራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህም ተቋማዊ ለውጥን በንድፈ-ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባራዊ ‘የማህበረሰብ አገልግሎት’ እና በማማከር ስራዎች ማረጋገጥ እንደሚቻል በተጨባጭ ያሳየ ስኬታማ ተሞክሮ ነው።

እንደ ደቡብ ኮሪያ ያሉ ሀገራትም የአመራር አካዳሚዎቻቸውን ከኢንዱስትሪው ፍላጎት ጋር በማስተሳሰር፣ በዲጂታል አስተዳደር (E-Governance) ዙሪያ የሚሰጡት ስልጠና ለኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነታቸው የጀርባ አጥንት ሆኗል። እነዚህ አካዳሚዎች የሚሰጡት ስልጠና በክፍል ውስጥ ንግግር ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ መሪዎች በቴክኖሎጂ የታገዘ የፖሊሲ ትንተና እንዲያደርጉና ውስብስብ ሀገራዊ ችግሮችን በምርምር እንዲፈቱ የሚያስችል ነው። ይህ በተግባር ላይ የተመሰረተ ትምህርት (Action Learning) አመራሩ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መፍትሔ እንዲያመነጭ ይረዳዋል።

የአመራር አካዳሚዎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለማማከር አገልግሎት ማዋላቸው ለተቋማዊ ብቃት ወሳኝ ሞተር ነው። ስልጠናን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና ከሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አቀናጅቶ መምራት፣ የተቋማትን የመፈጸም አቅም ከማሳደጉም በላይ የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ውጤታማ አመራር ለመፍጠር ብቸኛው መንገድ ነው። በመሆኑም፣ የእነዚህ አካዳሚዎች ሚና




ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ለ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂ ስኬታማነት እገዛ ያደርጋል

ከመደበኛ ትምህርት ባለፈ የሀገርን የወደፊት እጣ ፈንታ ወደ መቅረጽ የተሸጋገረ ስትራቴጂካዊ ተግባር ሆኗል።

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚም ይህንኑ እውን ለማድረግ ነው የተመሠረተው፤ አካዳሚው በሰለጠነ የሰው ኃይል ለስልጠና እና ምርምር አገልግሎት የሚውሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ለመንግስትና ለግል ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና፣ ችግር ፈቺ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር፣ የማማከር እና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማጎልበት አንዱ ዓላማው ነው። ለመሆኑ አካዳሚው ከተማዋ የተያያዘችው አገልግሎትን የማዘመን ጥረት እንዲሳካ ምን ድጋፍ ያደርጋል? ዲጂታል 2030 እውን እንዲሆን ከማገዝ አንጻርስ ምን እየሰራ ነው? የሚሉ ነጥቦችን በዚህ ፅሑፍ እንፈትሻለን፡፡

በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የሲስተም አድሚኒስትሬተር ከፍተኛ ባለሙያ ወይዘሮ ፅዮን ተስፋዬ አካዳሚው የከተማዋን አመራርና ባለሙያ በቴክኖሎጂ በማዘመን ረገድ የበኩሉም ሚና እየተወጣ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

አካዳሚው ስልጠናዎቹን በዘመናዊ የዲጂታል መድረኮች በማገዝ፣ ሰልጣኞች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለዕለት ተዕለት ተግባራቸው እንዲጠቀሙና የዲጂታል ባህል በየተቋማቱ እንዲሰርፅ እያደረገ ነው ያሉት ወይዘሮ ፅዮን፣ ይህ ጥረት አመራሩ የቴክኖሎጂን አስፈላጊነት ተገንዝቦ በየመሥሪያ ቤቱ የሚተገበሩ የዲጂታል አሰራሮችን በባለቤትነት እንዲመራና እንዲያስፈጽም ከፍተኛ አቅም እየፈጠረ ነው ሲሉ አክለዋል።

ኢትዮጵያ እየሄደችበት ያለው ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ራዕይን እውን እንዲሆን አካዳሚው የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ሲሆን፣ በተለይ የሰው ኃይል ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፤ የወደፊት መሪዎች በዳታ ትንተና፣ በሳይበር ደህንነት እና በዲጂታል ፖሊሲ ቀረጻ ላይ በቂ ክህሎት እንዲኖራቸው በማድረግ የዲጂታል ኢኮኖሚውን የሚመራ ብቁ ዜጋ እያፈራ ነው። ይህ ስትራቴጂካዊ ዝግጅት ከተማዋ የቴክኖሎጂ ባለቤት እንድትሆንና ሀገራዊ የዲጂታል ጉዞው ስኬታማ እንዲሆን ወሳኝ የሆነውን የአመራርና የባለሙያ አቅም ግንባታ ሚና እየተወጣ መሆኑን ያሳያል።

የ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂ፣ ኢትዮጵያ ካለችበት የዲጂታል ጅምር ወደ ላቀ የቴክኖሎጂ ደረጃ ለመሸጋገር የቀረጸችው የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ ነው። ይህ ስትራቴጂ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ የተደረገ ሲሆን፣ የ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025’ ስኬቶችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ እንደሆነ ተብራርቷል፡፡

‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂ ሀገሪቱ በቴክኖሎጂ የታገዘ አካታች የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት የነደፈችው ብሔራዊ ፍኖተ-ካርታ ነው። ይህ ስትራቴጂ ኢትዮጵያን በ2030 የዲጂታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ አራት ዋና ዋና ምሰሶዎች እና አራት አነቃቂ መስኮች ላይ ያተኩራል። አንዱ ምሰሶ ግብርናን ማዘመን ሲሆን ይህም፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ የግብርና መረጃ ልውውጥን ማጠናከር እና የምርት ሂደትን ማቀላጠፍ ይሆናል። በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በዲጂታል ትስስር ማጠናከር፣ የቱሪስት መስህቦች በዲጂታል አማራጮች ማስተዋወቅ፣ አገልግሎቱን ቀላል ማድረግ እና የወጪ ንግድ ሂደትን ማዘመን፣ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ የቴክኖሎጂ ዘርፎችን (ለምሳሌ የሶፍትዌር ልማት እና የቢዝነስ ሂደት አውትሶርሲንግ) ማስፋፋት ትኩረት ከሚደረግባቸው መካከል ይሆናሉ ተብሏል።

አስተማማኝ የኢንተርኔትና የኤሌክትሪክ አገልግሎትን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ማዳረስ፣ ብሔራዊ የዲጂታል መታወቂያ (Fayda) እና የኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ስርዓቶችን (እንደ ኢ-ብር እና ቴሌብር) ማጠናከር፣ የመንግስት አገልግሎቶችን ወደ ዲጂታል በመቀየር ግልጽነትና ቀልጣፋ አሠራር መፍጠር እና ዜጎች የቴክኖሎጂ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግና የግል መረጃ ደህንነትን የሚጠብቁ ሕጎችን ማውጣት የ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ መሠረቶች ይሆናሉ፡፡

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚን የመሰሉ ከተማ አቀፍ ተቋማት ደግሞ የየመዋቅሩን የሰው ኃይልና አሰራር ወደ ዲጂታል ዓለም የመቀየር ግብ ማስቀመጣቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ የ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂ ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ቀዳሚ የቴክኖሎጂ ማዕከል ማድረግና የዲጂታል ኢኮኖሚውን ለሀገር እድገት ዋነኛ ምሰሶ ማድረግ የሚል ሲሆን ይህ ውጥን እውን እዲሆን የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ወይዘሮ ፅዮን ተናግረዋል፡፡

‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂን እውን ከማድረግ አንፃር ከተቀመጡ አራት ዋና ዋና ምሶሶዎች አንዱ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት እንደመሆኑ ለዚህም ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው፡፡ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራርን በሰፊው ከመተግበር አኳያ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል ማለት ይቻላልም ብለዋል፡፡

የ‘ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030’ ስትራቴጂ ስኬት በቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ያንን ቴክኖሎጂ በሚመራውና በሚያስፈጽመው ሰው ተኮር አቅም ላይ የተመሰረተ ነው። የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ይህ ስትራቴጂ እውን እንዲሆን የተለያዩ ሚናዎችን ይጫወታል፡፡ በተለይ በዲጂታል አመራር ግንባታ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖራዋል፡፡ አመራሩ የዲጂታል አሰራርን እንደ አማራጭ ሳይሆን እንደ ግዴታ እንዲመለከት የማሳመን ስራ ይሰራል፣ በተጨማም መሪዎች በዳታ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ እንዲከተሉ ቴክኒካዊ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

የመንግስት አገልግሎቶች ወደ ዲጂታል ሲቀየሩ፣ እነሱን የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎች ብቁ መሆን አለባቸው። በሳይበር ደህንነት፣ በዲጂታል ፖሊሲ ቀረጻ እና በኢ-ገቨርናንስ ዙሪያ አካዳሚው ክፍተትን መሠረት ያደረገ ተከታታይ ስልጠናዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤ በየተቋማቱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ልምድ እንዲዳብር በምሳሌነት መሪዎችን ያበቃል።

ስትራቴጂው በወረቀት ላይ የሰፈረውን ያህል በተግባር እንዲተረጎም አካዳሚው በከተማዋ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያሉ ማነቆዎችን በመለየት፣ በቴክኖሎጂ እንዴት መፍታት እንደሚቻል ጥናታዊ መፍትሄ ማቅረብ ይኖርበታል። ተቋማት የዲጂታል አሰራርን ሲዘረጉ (ለምሳሌ፡ የወረቀት አልባ አሰራር) የቴክኒክና የአመራር ድጋፍ የመስጠት ሚናም ይኖረዋል፡፡

# ልጆች፤ ያላችሁን ተሰጥዖ ምን ያህል ታውቁታላችሁ?







ፎቶ- በገነት ወንድሙ

ከግራ ወደ ቀኝ ቤተልሔም ኃይልዬ ፣ ተመስገን ብዟየሁ እና ቴዎብስትያ ስንታየሁ

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች እንዴት ናችሁ? ምን ዓይነት ተሰጥኦ አላችሁ? ይህን ቀድሞ ማወቅ ለምን እንደሚጠቅም ለማወቅ በጥበብ ዕድገት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጎራ ብለናል፤ ተሰጥኦዋቸውን አውቀው ተግባር ላይ ያዋሉትን ልጆች ተሞክሮም ይዘንላችሁ ቀርበናል፤ መልካም ንባብ፡፡

ቴዎብስትያ ስንታየሁ እባላለሁ፤ 14 ዓመቴ ነው፡፡ ያለኝ ተሰጥኦ ሰርከስ ነው፡፡ ሰርከስ መሥራት ከጀመርኩ አራት ዓመት ሆኖኛል፡፡

ይህን ያደረግኩት ጓደኞቼ ቀድመው በጀመሩት ሰርከስና ባሳዩት ትርኢት በመነሳሳት ነው፡፡ ከዚያም ለቤተሰቦቼ ነግሬ ስፖርቱን ሰለጠንኩ፡፡

የምሠራቸው የሰርከስ ዓይነቶች የሰውነት መተጣጠፍ፣ ላይራ (መንጠላጠል)፣ ስኬት፣ ቲሹ፣ በባለአንድ እግር ሳይክል ጎማ ላይ ትርኢት ማሳየት ናቸው፡፡ በዚህም ባለፈው የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ ከትምህርት ቤቱ ተመርጬ ትርኢት አቅርቤያለሁ። በዚህም በጣም ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ያለኝን ተሰጥኦ ወድጄ እንድሠራ የተለያዩ ቁሳቁሶችን የሚያሟሉልኝ ቤተሰቦቼ እንዲሁም የሚያበረታቱኝ የቀለም እናትና አባቶቼ (መምህሮቼ) ናቸው፡፡ በዚህም ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

ስፖርቱን ስጀምር እንደ ጓደኞቼ ለመሥራት ነበር፡፡ አሁን ግን ፍላጎቴ እየጨመረ መጥቶ በሰርከሱ ዘርፍ የኢትዮጵያን ስም ማስጠራት እፈልጋለሁ።

ተሰጥዖን መከተል አላማን ለማሳካት ይጠቅማል፡፡ ይህ ተሰጥዖዬ በስራ አለም ስኬታማ እንድሆን እንደሚያግዘኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ በአሁኑ ወቅት ሰውነቴም እንዲጠነክርና ቀልጣፋ እንድሆን ረድቶኛል፡፡


ተመስገን ብዙአየሁ እባላለሁ። የ6ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 13 ዓመቴ ነው፡፡ ሥዕል የመሳል ተሰጥኦ አለኝ። ተራራና ሐይቅን ጨምሮ የተለያዩ ሥዕሎችን እሥላለሁ፡፡ የሥዕል ተሰጥኦዬን ለማሻሻል ከትምህርት ሰዓት ውጭ ያለውን ጊዜና ቅዳሜና እሁድን እጠቀማለሁ፡፡ መምህሮቼም የንድፍ ሥራ እንዴት እንደሚሠራ ያሳዩኛል፤ የተለያዩ ሥዕሎችን ሥዬ እንዳሳያቸው በማድረግም ያበረታቱኛል። የስዕል ተሰጥኦዬ በአሁኑ ወቅት የእጅ ጽሑፌ የተስተካከለ እንዲሆን አድርጎኛል፡፡

ቤተልሔም ኃይልዬ እባላለሁ፡፡ የተለያዩ ሥነ ጽሑፎችን እጽፋለሁ፡፡ በጥበብ ዕድገት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከናወኑ ሳምንታዊ ክንውኖችን መረጃ በመውሰድ፣ አስፍቼና አቀነባብሬ በዜና መልክ አነባለሁ፡፡

ግጥሞችንና መነባንቦችን ጽፌ አቀርባለሁ። በትምህርት ቤታችን "የእኛው ለእኛው" በተሰኘ መርሐ ግብር ላይ መምህራንን እና ተማሪዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግና በመጻፍ በየሳምንቱ ዓርብ ጠዋት 2፡30 ሰዓት አቀርባለሁ፡፡ የቴአትርና የፊልም ጽሑፎችን እየጻፍኩ ለትምህርት ቤቱ እሰጣለሁ፡፡

የሥነ ጽሑፍ ፍላጎቴ የጀመረው ከሦስተኛ ክፍል ጀምሮ ነው፡፡ የከበደ ሚካኤልን ግጥሞች ሳነብ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ "ቁጭ ብዬ ይህን ልጻፍ" ብዬ አቅጄ ጽፌ አላውቅም፤ የምጽፈው በድንገት ከምሰማው፣ ከማየው ወይም ከተከሰተው ነገር በመነሳት ነው። ይህ ፍላጎቴ እንዲጨምር ደግሞ ቤተሰቦቼ የተለያዩ የግጥም መጻሕፍትን እንዳነብብና የግጥም ርዕሶችን በመስጠት እንድጽፍ በማበረታታት ያግዙኛል። ይህን ተሰጥኦዬን በማሳደግ ወደፊት ጋዜጠኛ የመሆን ሕልም አለኝ፡፡

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ከውሀ ተፈጥሮ ፤ በውሃ የሚጠፋ**

**መልስ፡-** ሀ. ጨው

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**እግሩ አንድ ጭንቅላቱ ሦስት**

ሀ. መንሽ
ለ. ዶማ
ሐ. ቀንበር

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ወደ ተገልጋዩ የቀረበው አገልግሎት

- **በተንቀሳቃሽ አገልግሎት መስጫ አውቶብስ የሚሠራ ሙያተኛ ከአንድ በላይ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችል ዝግጅት እንደሚያደርግ ተጠቁሟል**

**በደረጀ ታደሰ**


ፎቶ- ከፋይል
የቀድሞው የአዲስ መሶብ ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ የተንቀሳቃሽ መሶብ አገልግሎት ዝግጅትን ሲጎበኙ

በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ፍልስፍና "ተገልጋዩ ወደ መንግስት ቢሮ" ከሚለው የቆየ አሠራር ወጥቶ፣ "አገልግሎቱ ዜጎች ወዳሉበት ስፍራ እንዲሄድ" ወደሚያደርግ ስር ነቀል ለውጥ እየተሸጋገረ ይገኛል። ይህን የተገበሩ እና እየተገበሩ ያሉ አገራት በርካታ ናቸው፡፡ ለአብነት ያክል፡- እንደ ኢስቶኒያ፣ ሲንጋፖር፣ ህንድ፣ አዘርባጃን የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ አገራት የመንግስት አገልግሎትን ወደ ዜጎቻቸው ለማድረስ ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂ እና አሠራር ተጠቅመዋል፡፡

ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ (99 በመቶ የሚሆነውን የመንግስት አገልግሎት) በዲጂታል አማራጭ ለዜጎቻቸው ተደራሽ በማድረግ በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀሰው ኢስቶኒያ፤ ለዚህ ውጤታማነት "ኤክስ-ሮድ(X-Road)" የተሰኘ የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ዘርግታለች፡፡ ቴክኖሎጂው ዜጎች የሞባይል ስልካቸውን በመጠቀም ካሉበት ሆነው የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ በምርጫ ወቅት ድምፅ እንዲሰጡ፣ የዲጂታል ፊርማን በመጠቀም ህጋዊ ሰነዶችን እንዲያጸድቁ እና ሌሎችንም መንግስታዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡

በተመሳሳይ የሲንጋፖር መንግስት ይፋ ባደረገው "ላይፍ.ኤስጂ (Life SG)" በተሰኘ መተግበሪያ አማካኝነት፣ ለዜጎች የተለያየ የመንግስት አገልግሎትን ባሉበት በማድረስ በተሞክሮነት የሚጠቀስ ሥርዓትን ገንብቷል። የሕንድ የዴልሂ ግዛትም "የመንግስት አገልግሎትን በተገልጋዮች በር ማድረስ (Doorstep Delivery of Public Services)" በተሰኘው መርሃ-ግብር፤ ለሥራው የሠለጠኑና የተመደቡ የመንግስት ተወካዮችን በማሰማራት እንደ መንጃ ፍቃድና መሰል ሰነዶችን ዜጎች ቤት ድረስ በመላክ በእጃቸው የሚደርስበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሰነባብቷል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ልዑካቸውን በመያዝ በቅርቡ አቅንተውባት የነበረችው፣ በምሥራቃዊ አውሮፓ የምትገኘው አዘርባጃን፣ የመንግስት አገልግሎትን የማዘመን ተሞክሮ ሌላኛው ተጠቃሽ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ቁልፍ ከተቋቋመ አሥራ አራት ዓመታትን ያስቆጠረው "አሳን ሰርቪስ (ASAN Service)" የተሰኘው የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተቋም ነው፡፡ ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት 15 የመንግሥት ተቋማትና 30 የግል ድርጅቶችን በአንድ ጣሪያ ስር በማሰባሰብ፣ ከ400 በላይ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። በዚህ ማዕከል ለአገልግሎት የሚመጡ ዜጎች ማንኛውንም መንግሥታዊ ጉዳይ በአማካይ በ17 ደቂቃ ውስጥ ብቻ እንዲያጠናቅቁ አስችሏል። ከዚህ በተጨማሪም፤ ቋሚ ማዕከላት በሌሉባቸው አካባቢዎች በተንቀሳቃሽ መኪናዎች በመጠቀም አገልግሎቱን ወደ ተገልጋዩ ተደራሽ በማድረግ ላይ ትገኛለች።

ከላይ በምሳሌነት ያነሳናቸው አገራት የመንግስት አገልግሎቶችን ወደ ዜጎች ለማድረስ የተጓዙበት ርቀት እና ያስመዘገቡት ውጤት እንደየአገራቱ ይለያያል፡፡ ይህም ሆኖ፤ ወቅቱ "ተገልጋዩ ወደ መንግስት ቢሮ" የሚለውን የቆየ ፍልስፍና፣ "የመንግስት አገልግሎቶችን ወደ ዜጎች መውሰድ" በሚል በመለወጥ ላይ ተመሳሳይ መርህና መንገድን በመከተል ላይ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያም ይህንኑ የአሠራር መርህ በመከተል፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን እያስመዘገበች ትገኛለች። በተለይ "የመሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት" መቋቋምና ለአገልግሎት መብቃትን ተከትሎ የመጣው መነቃቃት፣ በምሳሌነት የጠቀስናቸው አገራትን በሩቅ ከመከተል አልፎ፣ ተፎካካሪና ተወዳዳሪ መሆን ወደሚያስችል ደረጃ እንደሚያደርስ መገመት ለትችት የሚዳርግ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ መዲና ከሆነችው አዲስ አበባ እቅፍ ውስጥ ሆኖ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገልግሎት አሰጣጡ ዝማኔ እንደፀሐይ ጮራ እየፈካ የመጣው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት (Addis MESOB - One Center Digital Government Service) ውጤታማነት ከከተማ አስተዳደሩ ተሻግሮ ለሌሎች የአገሪቷ አካባቢዎች የልምድ መቅሰሚያ ማዕከል ሆኗል፡፡ ጳጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በይፋ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው ማዕከሉ፣ በሂደት የቦሌ ቅርንጫፍን በመጨመር ለከተማዋ ነዋሪዎች ከ140 በላይ አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡ የካቲት 21 ቀን 2018 ዓ.ም ተቋሙ ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት፤ በወራት ዕድሜ ውስጥ በዋናው መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ አማካኝነት 100 ሺህ ለሚደርሱ ተገልጋዮች አገልግሎት አድርሷል። ተገልጋዮችም ባገኙት አገልግሎት ከፍተኛ እርካታ እንደተሰማቸው፣ ተቋሙ በዲጂታል ቴክኖሎጂ በታገዘ የእርካታ ልኬት ጥናት መሠረት አማካይ የተገልጋይ እርካታ 98 በመቶ ወይም እጅግ ከፍተኛ ሆኖ መመዝገቡን አሳውቋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ በወርሃ ጥር መጨረሻ አካባቢ፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመገኘት የ2018 በጀት ዓመት የስድስት ወራት አፈፃፀም ሪፖርት በማቅረብ፣ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአባላት ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት፣ የመንግስት አገልግሎትን ለዜጎች በጥራት፣ በፍጥነትና በፍትሐዊነት ለማድረስ ለተቀመጠው አገራዊ ዓላማ የመሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑን መስክረዋል። አያይዘውም፤ የመሶብ አገልግሎት በተንቀሳቃሽ አውቶብስ አማካኝነት ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን መግለፃቸው ይታወሳል። በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተላለፈውን አገር አቀፍ አቅጣጫ መነሻ በማድረግ በተንቀሳቃሽ አውቶብስ በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ልዩ ስፍራ አገልግሎት ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ በከተማው 5ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ ለምክር ቤት አባላት አሳውቀዋል፡፡

በዚሁ መሠረት የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ወደ ሥራ ካስገባቸው ሁለት መደበኛ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት በተጨማሪ፤ ለነዋሪው ተደራሽ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን ዝግጅት የጀመረው ወዲያው ነበር። ለዚህ የሚያግዙ ተንቀሳቃሽ አውቶብሶችን ለአገልግሎቱ በሚመች መልኩ የማዘጋጀት፣ ሙያተኛዎችን የማብቃት እና ተያያዥ ተግባራትን የመከወኑን ሥራ የአዲስ መሶብ አመራሮች እና የሚመለከታቸው አካላት ማቀላጠፋቸውን ቀጥለዋል፡፡ ሥራው ወደ መጨረሻ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝም፤ የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በቅርቡ (ማለትም የካቲት 21 ቀን 2018 ዓ.ም.) ባደረጉት የሥራ ጉብኝት እና በሰጡት መረጃ አረጋግጠዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተንቀሳቃሽ አውቶብስ አማካኝነት በከተማዋ ልዩ ልዩ ስፍራዎች አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችለው ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝ እስከ የካቲት 25 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተቋም ዋና ዳይሬክተር ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩት፤ ከየካቲት 25/2018 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመሶብ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆነው እንዲያገለግሉ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተሾሙት አቶ ዮናስ አለማየሁ መግለፃቸው ይታወሳል። በጉብኝቱ ወቅት እንዳብራሩት፤ ከሰው ሃይል እና ቴክኖሎጂ ዝግጅት በተጨማሪ የተንቀሳቃሽ አገልግሎት መስጫ አውቶብስ የሜካኒካል ስራ እየተገባደደ ይገኛል፡፡ በአገልግሎት መስጫ አውቶብሶቹ ውስጥ ስምንት የአገልግሎት መስጫ መስኮቶች ተካትተዋል። ተቋሙ በሚያዘጋጀው ባስ ላይ ሥራቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከ20 በላይ አገልግሎቶች ተለይተዋል። እነዚህ የተመረጡት አገልግሎቶች ኅብረተሰቡ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ከሚያስፈልጉት ዋና ዋና የመንግስት አገልግሎቶች መካከል ቀዳሚዎቹ የተባሉት ናቸው። በተንቀሳቃሽ አገልግሎት መስጫ አውቶብስ ላይ የሚሠራ አንድ የደምበኛ አገልግሎት ሙያተኛ ከአንድ በላይ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችል የሙያ ዝግጅት እንደሚያደርግ ታውቋል።

በአጠቃላይ የአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን ጨምሮ እንደ አገር እየተስፋፋ ያለው በአንድ ማዕከል ተገልጋይን በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ የማስተናገድ ጉዳይ ፍጥነትን፣ ጥራትን፣ ፍትሐዊነትን፣ ከአድሎና ከሙስና በፀዳ መልኩ ወደ ተገልጋዮች መድረስን ከማጠናከር አንጻር የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው እና መሰል አገራት ተሞክሮ የሚያሳየውም ይህንኑ ሀቅ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ምክንያቱም የተቀናጀ የዲጂታል ስርዓትን መዘርጋትና አገልግሎትን ወደ ቤት እና ደጃፍ ማድረስ የመንግስት ቢሮክራሲን ከማቃለሉም በላይ ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ከማዕከል ርቀው ለሚገኙ ነዋሪዎች ምቹ የሆነ የመንግስት አገልግሎት ለመስጠት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ስለዚህ ጅምሮችን አጠናክሮና አስፋፍቶ ማስቀጠል ይገባል፡፡

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# የከተማ ግብርና ለስራ እድል ፈጠራው ያለው አበርክቶ

- **በአዲስ አበባ ከተማ በተያዘው በጀት ዓመት በ8 ወር ውስጥ ብቻ በከተማ ግብርና ለ20 ሺህ 455 ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩ ተገልጿል**

**በይግለጡ ጓዴ**

የከተማ ግብርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከምግብ ዋስትና ባለፈ፣ ፈጣን የሥራ ዕድል መፍጠሪያና የከተሞች የኢኮኖሚ ሞተር እየሆነ መጥቷል። በተባበሩት መንግሥታት የግብርና እና ምግብ ድርጅት (ፋኦ) መረጃ መሠረት፣ በዓለም ዙሪያ ከ800 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በከተማ ግብርና ተግባራት ላይ የተሰማሩ ሲሆን፣ ይህም ለከተማ ነዋሪዎች የገቢ ምንጭ ከመሆን ባለፈ ለወጣቶችና ለሴቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ከፍቷል። ዘርፉ ከምርት እስከ ገበያ ባለው ሰንሰለት ውስጥ በሚፈጥረው የሥራ ዕድል፣ የከተሞችን የሥራ አጥነት ጫና በመቀነስ ረገድ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

በዚህ ረገድ እንደ ኩባዋ ሃቫና፣ ሲንጋፖር እና ሲያትል ከተሞች ተጠቃሽ የዓለም ተሞክሮዎች ናቸው። ለምሳሌ በሃቫና የከተማዋን የአትክልትና ፍራፍሬ ፍላጎት 90 በመቶ የሚሸፍነው ይኸው ዘርፍ ሲሆን፣ ከ300 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። ሲንጋፖር ደግሞ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑትን የጣራ ላይ እና የቤት ውስጥ እርሻዎችን (የሽቅብ እርሻ) በመጠቀም፣ ውስን መሬትን ለከፍተኛ የሥራ ዕድልና ለምርት ምንጭነት በማዋል ረገድ ቀዳሚዋ ከተማ ሆናለች።

እነዚህ ከተሞች ከዘርፉ ያገኙት ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው፤ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር፣ የምግብ ትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ የዋጋ ንረትን መቆጣጠር አስችሏቸዋል። በተጨማሪም፣ የከተማ ግብርና አረንጓዴ ልማትን በማስፋፋት የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና የከተማን ውበት ለመጠበቅ ትልቅ ፋይዳ አለው። ይህም የከተማ ግብርና ለዘላቂ ልማትና ለጠንካራ የከተማ ኢኮኖሚ ግንባታ መሠረት መሆኑን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተግባር ተረጋግጧል።

ከላይ በጠቃቀስናቸው መረጃዎች መሠረት፣ የከተማ ግብርና በዘመናዊ ከተሞች ውስጥ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ ዘርፍ በተለይ ለወጣቶችና ለሴቶች አዳዲስ የገቢ ምንጮችን ለመክፈት ትልቅ አቅም አለው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት በሚያስችለው አግባብ ተደራጅቶ በመንቀሳቀስ ተጨባጭ ለውጦችን እያስመዘገበ ይገኛል። የከተማ ግብርናን በከተማዋ የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ሂደት ድርሻውን ከማሳደግ አንጻር፣ በመደበኛና በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ ሥራ በማጠናከር በዘርፉ የከተማዋ ማህበረሰብ በብዛት ከተማ



ፎቶ- ከፋይል

በከተማዋ የስራ ዕድል ፈጠራ ተግባር ውስጥ የከተማ ግብርና ከፍተኛ ሚና አለው

ግብርና እንዲሳተፍ ማድረግ ተችሏል። በዚህም ነባር የከተማ ግብርና ተጠቃሚዎችን በማስቀጠልና አዳዲስ ተሳታፊዎችንም ወደ ዘርፉ በማስገባት ሰፊ ሥራ ተሠርቷል።

ኮሚሽኑ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ የከተማዋን ነዋሪዎች በከተማ ግብርና ዘርፍ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ነው። በከተማዋ በርካታ ነዋሪዎች በዶሮና በወተት ላም እርባታ፣ በከብት ማድለብ፣ በንብ ማነብ፣ በሰብል እና በሌሎችም ዘርፎች ተደራጅተው በመሥራት ውጤታማ እየሆኑ መጥተዋል። ነዋሪዎች በመኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ እና ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በከተማ ግብርና ዘርፍ በመሰማራት የምግብ ፍጆታቸውን መሸፈን ችለዋል።

አቶ አረጋ ታደሰ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ነዋሪ ሲሆኑ፣ በዶሮ እርባታ ዘርፍ ተሰማርተው ተጠቃሚ ሆነዋል። የአካል ጉዳተኝነት ተግቶ ከመሥራት ያልገደባቸው አቶ አረጋ፣ በመኖሪያ ቤታቸው ባለቻቸው ውስን ቦታ የዶሮ ኬጆችን (Cages) በመሥራት ከአንድ ዓመት ወዲህ ወደ ሥራ እንደገቡ ይናገራሉ።

ዶሮ የማርባት የቆየ ፍላጎት እንደነበራቸው የሚያስታውሱት አቶ አረጋ፣ ከሚያውቋቸው ሰዎችና ከቤተሰቦቻቸው ባገኙት የገንዘብ ድጋፍ የመኖሪያ ቤታቸውን ከፍለው የዶሮ ቤት በመሥራት ወደ ሥራ ገብተዋል። ከክፍለ ከተማው አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤት ድጋፍ በተሰጣቸው 65 የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች ሥራውን መጀመራቸውን ገልጸዋል።

አቶ ጌታቸው ነጠረ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የጣሊያን ኤምባሲ አካባቢ ነዋሪ ናቸው። ማዕዛ ጌታቸውና ጓደኞቿ የንብ እርባታ ሽርክና ማህበር በማቋቋም፣ አምስት ሆነው በመደራጀት በሌማት ትሩፋት በንብ ማነብ ዘርፍ ከሁለት ዓመት ወዲህ ጀምሮ ወደ ሥራ እንደገቡ ገልጸዋል።

በከተማ ግብርና ኮምፖስት በማዘጋጀት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው አቶ ጥላሁን ጴጥሮስ እና ጓደኞቻቸው 10 አባላት ሆነው በመደራጀት በእንስሳት ተረፈ ምርት ኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) እያዘጋጁ ለተጠቃሚዎች ያቀርባሉ። ሂደቱን ጠብቆ የተዘጋጀውን ኮምፖስት በከተማ ግብርና እና በአረንጓዴ ልማት እንክብካቤ ሥራ ለተደራጁ ማህበራት እንደሚያስረክቡ ተናግረዋል። በኮምፖስት ዝግጅት የሥራ ዕድል በመፍጠር ገቢን ማሳደግ መቻላቸውን አቶ ጥላሁን ገልጸዋል።

በዶሮ እርባታ ሥራ ላይ የተሰማሩት አቶ ተስፋዬ አትርፎ እና ወይዘሮ ፅጌ ደፋሩ፤ በተመቻቸላቸው የብድርና የቴክኒክ ድጋፍ የሥራ ዕድል በመፍጠር እንቁላል ለገበያ በማቅረብ የገቢ አቅማቸውን እያሳደጉ መሆኑን ገልጸዋል።

የከተማ ግብርና በትንሽ ቦታ ላይ በዘመናዊ መንገድ አትክልቶችን በማምረት ለገበያ ማቅረብ ያስችላል። የከተማ አካባቢን ባገናዘበ መልኩ የዶሮ እርባታ፣ የንብ ማነብ እና የዓሳ እርባታ ሥራዎችን መሥራት እንዲሁም ለቤት ውስጥ እና ለቢሮ ውበት የሚሆኑ ዕፅዋትን በማፍላትና በመሸጥ የሥራ ዕድል እየተፈጠረ ይገኛል።

የሚመረቱ የግብርና ውጤቶችን በማጠብ፣ በመቁረጥ፣ በማሸግ ወይም ወደ ሌላ ምርት በመቀየር እሴት ጨምሮ በመሸጥ የሥራ ዕድል መፍጠር ይቻላል። ከአምራቹ በቀጥታ ለተጠቃሚው የሚያደርሱ የዲጂታል ገበያ መድረኮችን ወይም አነስተኛ መሸጫዎችን መፍጠር ሌላኛው የከተማ ግብርና ጥቅም ነው።

የተሻሻሉ ዘሮችን፣ ማዳበሪያዎችን እና አነስተኛ የግብርና መሣሪያዎችን የሚያቀርቡ ጥቃቅን ተቋማት እንዲሁም ለግለሰቦች ወይም ለድርጅቶች የጓሮ እርሻ ወይም የጣራ ላይ እርሻ የሚሠሩ ባለሙያዎች ይገኙበታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃ እንደሚያመላክተው፣ በ2017 በጀት ዓመት በከተማ ግብርና ዘርፍ ለ25 ሺህ 221 ወጣቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፤ ከእነዚህም መካከል 14 ሺህ 733 በእንቁላል ጣይ ዶሮ፣ 5 ሺህ 957 በእፅዋት ሀብት ልማት፣ 5 ሺህ 646 በአትክልት ልማት፣ 1 ሺህ 740 በወተት ከብት እርባታ፣ 1 ሺህ 328 በዳልጋ ከብት ማድለብ፣ 709 በበግ ማድለብ እና 341 በንብ ማነብ ከተፈጠሩት የሥራ ዕድሎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

በተያዘው በጀት ዓመት በ8 ወር ውስጥ ብቻ በከተማ ግብርና ለ20 ሺህ 455 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። ይህም ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ከተማ ግብርና ዘርፍ እየገቡ ያሉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑን ያሳያል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ቢንያም ገለጻ፣ የሥራ ዕድል ሊፈጠርባቸው የሚችሉ ጸጋዎችን የመለየት፣ የኮሚሽኑ የድጋፍ እና ክትትል ባለሙያዎች እስከ ወረዳ ድረስ በመውረድ ሥራውን የመከታተልና የመደገፍ ሥራ ይሠራሉ።

ተግባሩን ለማሳካት ከሚያግዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ዕቅዱን የጋራ በማድረግ ወደ ተግባር ተገብቷል። የሥራ ዕድል ፈጠራው የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ በሳምንት ሁለት ጊዜ የግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ከሌማት ትሩፋት ንቅናቄ ሥራ ጋር በማስተሳሰር ከክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች እና ከማዕከል ደጋፊ ባለሙያዎች ጋር ግምገማ ይደረጋል።

በእንቁላል ጣይ ዶሮ፣ በጫጩት ማሳደግ (ለእንቁላል ጣይ ደሮ)፣ በጫጩት ማሳደግ(ለስጋ)፣ በወተት ከብት እርባታ፣ በዳልጋ ከብት ማድለብ፣ በበግ ማድለብ፣ በንብ ማነብ፣ በዓሳ እርባታና በእንስሳት መኖ ማቀነባበር የሥራ ዕድል ከተፈጠረባቸው ዘርፎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ኢነርጂ ቆጣቢ ብልሃቶች

- **በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት በ15 ተቋማት ላይ የኢነርጂ ኦዲት ተደርጓል**

**በለይላ መሀመድ**

ከሀይል አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ኢነርጂ ኦዲት እንደሚደረግ ምን ያህሎቻችን እናውቃለን፡፡ ለመሆኑ የኢነርጂ ኦዲት ማለት ምን ማለት ነው? እንዴት ነው ኦዲት የሚደረገው? እነዚህንና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካል ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

አቶ መላኩ ጋሪ ይባላሉ፡፡ በተቋሙ የአየር ንብረት ለውጥ እና አማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የኢነርጂ ኦዲት እና ፈቃድ ቡድን መሪ ናቸው፡፡ በጉዳዩ ላይ በሰጡት ማብራሪያ፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የአካባቢ አየር ብክለትን እና የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት፣ አማራጭ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅና በማስረጽ እንዲስፋፉ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል የኤሌክትሪክ ሀይል ተጠቃሚዎችን እንዲሁም አምራች ተቋማትን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሀይል እንዳይባክን መስራት አንዱ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሀይል ቆጣቢ የሆኑ አማራጭ ኢነርጂዎችን እንዲጠቀሙ በተለያዩ ተቋማት ላይ የኢነርጂ ኦዲት ስራ ይሰራል፡፡

የኢነርጂ ኦዲት ማለት ስለአንድ ደንበኛ የኢነርጂ አጠቃቀም በቂ እውቀት ለማግኘት አዋጭ የሆኑ የኢነርጂ ቁጠባ እድሎችን መጠናቸውን በመለካት የተለያዩ ግኝቶችን ለማግኘት የሚደረግ የተቀናጀ የሪፖርት አሰራር ነው፡፡ የተለያየ የኢነርጂ ኦዲት አይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም ቅኝት፣ ዝርዝር እና ድንገተኛ ሜትር ፍተሻ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ቅኝት በመባል የሚታወቀው የኦዲት አይነት የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃትን ለመለየት መጠይቅ አዘጋጅቶ በመላክ ወይም በቦታው ተገኝቶ ተቋማት ላይ የሚባክነውን የኢነርጂ አይነት ልኬት መረጃ በመሰብሰብ ንጽጽር ትንተና ተሰርቶ የምናገኘው ውጤት ነው። ያለ መሳሪያ በአይን በማየት ኦዲት የሚደረግበት የኦዲት አይነት ነው፡፡

ዝርዝር የኢነርጂ ኦዲት የሚባለው የተሟላ የኢነርጂ ብቃትን ለይቶ ልኬቶችን በመውሰድና መሳሪያ በመጠቀም መረጃዎችን የሚሰበስብ ነው፡፡ እንደ ቅኝት ኢነርጂ ኦዲት ትንተና ተሰርቶ የሚባክነውን ሀይል ማግኘት የሚቻልበት ዘዴ ነው። ዝርዝር የኢነርጂ ኦዲት ለመስራት ጅምር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መሳሪያ እና የሰለጠነ ባለሙያ ስለማይገኝ እየተሰራበት አይደለም። ድንገተኛ የኢነርጂ ኦዲት ያረጁ እቃዎች ላይ በድንገት የሚሰራ ነው። ለምሳሌ፡- የተበላሸ ትራንስፎርመር ላይ በድንገት በመሄድ እንደሚሰራ ቡድን መሪው አቶ መላኩ ገለጸዋል።



ፎቶ- ከፋይል

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀይል ብክነትን ለመቀነስ ሀይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ያሰራጫል፤ የኢነርጂ ኦዲትም ያደርጋል

## ምን እየተሰራ ነው? ምን ውጤትስ ተገኝቷል?

ቡድን መሪው እንደገለፁት፣ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከ2012 ዓ.ም እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ የኢነርጂ ኦዲት ስራ እየሰራ ነው። በዚህም 100 በሚሆኑ ተቋማት ላይ ቅኝት ኢነርጂ ኦዲት ተሰርቷል፡፡ በዚህም ከ2 ሚሊየን 234 ሺህ 800 ኪሎ ዋት ሰዓት በላይ ኢነርጂ እየባከነ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። ይህ ወደ ክፍያ ሲቀየር 5 ሚሊየን ብር ይሆናል፡፡ የዚህ ዋና ችግር ብቃት ያላቸው አምፖሎችን፣ ምጣዶችንና ሌሎች ኤሌክትሮኒክ እቃዎችን ባለመጠቀም የመጣ ብክነት ነው፡፡

የኢነርጂ ኦዲት ሲሰራ የታዩ የተለያዩ ግኝቶች አሉ፡፡ የኢነርጂ ቁጠባ ፋይዳ በተለያዩ ተቋማት ብዙ ትኩረት ያለማግኘት፤ ግብረመልሶች ሲሰጣቸው አስገዳጅ ህግ ባለመኖሩ ምክንያት በተለይም የመንግስት ተቋማት ያለመስማትና ያለመቀበል ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- አምፖሎችን በማይጠቀሙበት ወቅት ያለማጥፋት፣ በቀን በርና መስኮቶችን ከመክፈት ይልቅ አምፖሎችን የማብራት ችግሮች በተለያዩ ተቋማት ይታያል። የመብራት ፍሎረሰንቶች ብልሽት እና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ሲቆሸሹም የሀይል ብክነት ያስከትላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የተለያዩ ተቋማት የመብራት ፍሎረሰንቶች ብልሽት ሲያጋጥም ያለማንሳትና ያለመቀየር ችግርም አለ፡፡ የተበላሸው ካልተነሳ ወይም ካልተቀየረ ሀይል ያባክናል፡፡ ይህ በብዙ ተቋማት የሚታይ ችግር ነው። እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ሲቆሸሹ የሀይል ብክነት ስለሚያስከትሉ ማጽዳት ያስፈልጋል፡፡ ኮምፒዩተሮች ሲያረጁ ከፍተኛ ኢነርጂ ስለሚጠቀሙ የሀይል ብክነት ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ እንደነዚህ አይነት ነገሮች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ኢነርጂን መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡

በተያዘው በጀት ግማሽ ዓመት በ15 ተቋማት ላይ የኢነርጂ ኦዲት ተደርጓል። ከ15ቱ 8ቱ የእንጀራ ጋጋሪዎች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ተቋማቱ ኦዲት ሲባል ለክፍያ ወይም ከግብር ጋር በማገናኘት በጥርጣሬ የማየትና ግኝቱን ያለመቀበል ችግር ተስተውሎ ነበር። 'የሚወጣውን ሐይል መቀነስ ለናንተም ወጪን ለመቆጠብ ይረዳችኋል' በሚል ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በመስራቱ ዓላማውን እንዲረዱት ማድረግ መቻሉን ቡድን መሪው ገልጸዋል፡፡

## የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት ምንድ ነው?

እንደ ቡድን መሪው አቶ መላኩ ገለጻ፤ የኢነርጂ ቁጠባ ማለት ኢኮኖሚያዊና በአንድ ሂደት ወይም ስርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ኢነርጂ መጠን ብክነትን በማስወገድ አግባብነት ባለው መልኩ የኢነርጂ አጠቃቀምን መቀነስ ማለት ነው። የኢነርጂ ኦዲት ተሰርቶ የሚባክነው ሀይል ከታየ በኋላ እንዲቆጥቡ ባለስልጣኑ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡

ሌላው ከኢነርጂ አጠቃቀም ጋር የሚነሳው የኢነርጂ ብቃት ነው፡፡ የኢነርጂ ብቃት ማለት አንድ በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰራ መሳሪያ የሀይል ፍጆታውን እንዲቆጥብ ማድረግ መቻል ወይም በሌላ አገላለጽ በተመሳሳይ ኢነርጂ ከፍ ያለ ምርት ወይም አገልግሎት የመስጠት ብቃት የሚለካበት ማለት ነው፡፡ ከፍ ያለ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ መሳሪያው ብቃት አለው ይባላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ምጣድ በተመሳሳይ ኢነርጂ ወይም ዝቅተኛ ኢነርጂን በመጠቀም ብዙ አገልግሎትን የሚሰጥ ከሆነ ብቃት አለው እንላለን፡፡ አምፖሎችን ጨምሮ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ብቃት አላቸው የምንለው በጥቂት ኢነርጂ ብዙ አገልግሎት መስጠት ሲችሉ ነው፡፡

## የኢነርጂ ብክነትን ለመከላከል የተወሰደ መፍትሔ

የተቋማትን የሀይል ብክነት ከማሻሻል ወይም ዘላቂ መፍትሄ ከማበጀት አንጻር ባለስልጣኑ የተለያዩ ስራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ አቶ መላኩ ያነሳሉ። በዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በዓለም ያሉ ከተሞችን በማቀፍ የሚሰራው C40 የተሰኘ ድርጅት በኢነርጂ አጠቃቀም ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች ተጠንተዋል፤ በባለስልጣኑ ባለሙያዎችም የቅኝት ኢነርጂ ኦዲት ስራዎች ተሰርተዋል። ሆስፒታሎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የምገባ ማእከላት ጨምሮ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ላይ ያሉ የኢነርጂ አጠቃቀም ችግሮች በጥናቶቹ እና በቅኝት ኢነርጂ ኦዲት ስራዎች እንዲለዩ በማድረግ የሚባክኑ ኢነርጂዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች እየተከናወነ ይገኛል።

በከተማ አስተዳደር በጀት ለሚተዳደሩ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች ሰርኩላር ደብዳቤ የማዘጋጀት ስራዎች ተሰርተዋል። 'ጂ አይ ዜድ' ከተባለ ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመነጋገር ለምገባ ማእከላት እና በሴፍቲኔት ለተደራጁ ማህበራት ድጋፍ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት ሀይል ቆጣቢ የሆኑ 220 የኤሌክትሪክ ምድጃዎች፣ 220 የቡና ማፍያ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች፣ 1 ሺህ 100 የኤሌክትሪክ ምጣዶችን በሁሉም ክፍለ ከተሞች ለማከፋፈል የግዢ ጨረታ ወጥቶ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 3ኛ እና 4ኛ ሩብ ዓመቱ 440 ሃይል ቆጣቢ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች እና 1 ሺህ የኤሌክትሪክ ምጣዶችን የማሰራጨት ስራ ይሰራል፡፡ በዚህም 1 ሚሊዮን 182 ሺህ 600 ኪሎ ዋት ሰዓት ዓመታዊ ኢነርጂ መቆጠብ ይቻላል፡፡ ይህም ወደ ብር ሲቀየር ወደ 6 ሚሊየን 30 ሺህ ብር ማዳን ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 220 በከሰል የሚሰሩ ምድጃዎች ወደ የኤሌክትሪክ ቡና ማፊያ ማሽን እና ስቶቭ በመቀየር ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቅን ወደ 26 ሺህ 100 ቶን Co2e( carbon dioxideemission) በካይ ጋዝ መቀነስ ያስችላል፡፡

አቶ መላኩ በግለሰብ ደረጃ በሀይል አጠቃቀም ረገድ የሚባክኑ ኢነርጂዎችን ለመከላከል የሚቻልበትን ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ የምግብ ማብሰያዎችን (ስቶቭ) ከተጠቀመ በኋላ ማጥፋትና ሶኬት መንቀል ይኖርበታል፡፡ ሌላው እንደ ቴሌቪዥንና ኮምፒዩተር ያሉ የኤክትሮኒክስ እቃዎችን በቤት ውስጥም ሆነ ቢሮዎች ላይ በማንጠቀምበት ወቅት ማጥፋት ያስፈልጋል፡፡ ቀን ላይ በተለይም ቤት ውስጥ አምፖሎችን ማጥፋት፣ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ማጽዳትና ሲበላሹ በፍጥነት ማሰራትና ማስጠገን ይገባል፡፡ ብቃት ያላቸውን የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች መግዛትና መጠቀም፣ ስቶቭና ምጣድ ለሀይል ብክነት ዋነኛ መንስኤዎች ስለሆኑ ብቃት ያላቸውን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የሚባክነው ኢነርጂ የሀገር ሀብት በመሆኑ የህግ ማእቀፍ ኖሮት ኢነርጂን በተገቢው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ለኢንዱስትሪ፤ መብራት ላላገኘው የገጠሩ ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ እና ደን እየጨፈጨፉ ለሚጠቀሙ የማህበረሰብ ክፍሎችንም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ በጥቅሉ ኢነርጂ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል ከማድረግ ባለፈ ብክነቱንም በማስቀረት ረገድ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

## የጨረታ ቁጥር፡- 005/2018 ዓ.ም

የአ/ቃ/ክ/ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል የመንግስት ግዥ ቡድን ለሴክተሮች የሚያሰፈልጉ የስፖርት ትጥቅ፤ ቋሚ አላቂ ዕቃዎች፤ የደንብ ልብስ እና ጫማዎች/፤ የፈርኒቸር ጥገና እና የመኪና ጎማ ግዥ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1፡- የስፖርት ትጥቅ ግዥ

ሎት 2፡- ቋሚ አላቂ ዕቃዎች ግዥ

ሎት 3፡- የደንብ ልብስ እና ጫማዎች

ሎት 4፡- የቢሮ ፈርኒቸሮች ጥገና

ሎት 5፡- የመኪና ጎማ

ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ይጋብዛል፡፡

1. በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ
2. የንግድ ምዝገባ ፍቃድ ያለው
3. የዘመን ግብር የከፈሉና በአቅራቢነት የተመዘገቡ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. ቫት ተመዝጋቢ የሆኑ
5. የጨረታ ማስከበሪያ CPO

ሎት 1፡- 50,000.00 / ሃምሳ ሺ ብር ብቻ /

ሎት 2፡- 5,000.00 / አምስት ሺ ብር ብቻ /

ሎት 3፡- 10,000.00 / አስር ሺ ብር ብቻ /

ሎት 4፡- 10,000.00 / አስር ሺ ብር ብቻ /

ሎት 5፡- 15,000.00 / አስራ አምስት ሺ ብር ብቻ /

**ሲፒኦ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል**
**አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት በሚል ያሰራሉ።**

ተጫራቾች የማይመለስ 200.00 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል እንዲሁም በጥቃቅንና አነስተኛ ለሚወዳደሩ ተጫራቾች በሀገር ዉስጥ ምርት ላይ ብቻ የተሳተፉ እና ካደራጃቸው አካል ስድስት ወር ያልሞላዉ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ በነፃ መውሰድ የሚችሉ ሲሆን ይህ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል የመንግስት ግዢ አስተዳደር ቡድን ሁለተኛ ፎቅ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡

6. የአሸናፊዉ ድርጅት CPO ተመላሽ የሚሆነዉ የዉል ማስከበሪያ የአጠቃላይ ያሸነፈበትን ዋጋ 10% ሲያሲዝ ብቻ ነዉ፡፡

7. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ ከመስሪያ ቤቱ በገዙት ዋጋ ማቅረቢያ ብቻ በግልጽ እና በሚታይመልኩ ያለ ስርዝ ድልዝ በመሙላት ኦርጅናል እና ፎቶ ኮፒውን በተለያ የፖስታ በማሸግ ሁለት ፖስታ በአንድ ላይ በታሸገ ኤንቨሎፕ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር (10) የሥራ ቀናት እስከ 11፡30 ሰዓት ሰነዱን መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

8. በአስራ አንደኛው (11) የስራ ቀን ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 4፡00 ሰዓት ተጫራጮች ሰነድ በማስገባት 4፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ ልክ 4፡30 ባለቤቱ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሁለተኛ ፎቅ ጨረታው ይከፈታል፡፡

9. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡-** አድራሻ ከቃሊቲ መናኸሪያ ፊት ለፊት ባለው የአስተዳደር ህንፃ ላይ ሁለተኛ ፎቅ መጠየቅ ይችላሉ፡

10. ናሙና ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ከጨረታ ሰነድ ጋር ለቢሮ ገቢ ማድረግ አለባችሁ፡፡

**የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል**
**የአስተዳደርና ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት ክብነሽ ዘውዴ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ቀበሌ ወይም በቀድሞው ወረዳ ---- የቤት ቁጥር የካርታ ቁጥር የካ/11/00/157/12 ሴሪ ቁጥር 07229027 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እየሩሳሌም ይርጋ ቦሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ ልዩ መለያ ኮዱ A000060807315 የሆነው ይዞታ እና በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የግዥው መለያ ቁጥር 002/18
## ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ፅ/ቤት ስር የሚገኘው የደጃ/ዘርዓይ ደረስ የመ/ደ/ ት/ቤት እና ጎላ ብርሃን አፀደ ህፃናት ት/ቤት በግልጽ ጨረታ ጊዥዎችን መፈጸም ይፈልጋል

1. የደንብ ልብስ እና የደንብ ልብስ ስፌት
2. አላቂ የቢሮ ዕቃዎች
3. አላቂ የህክምና ዕቃዎች
4. አላቂ የት/ት ዕቃዎች
5. የፅዳት ዕቃዎች
6. ልዩ ልዩ መሳሪያዎች
7. ፕላንትና ማሽነሪ እና መሳሪያ መግዣ
8. ህንፃና ቁሳቁስና ተገጣጣሚ ዕቃዎች

የተለያዮ ዕቃዎችን በግልፅ ጨረታ ላይ አወዳድሮ ለመግዛት ስለሚፈልግ በዚህ ዘርፍ የተሰማራቹ ድርጅቶች በጨረታው እንድትሳተፉ እየጋበዝን፡፡

**ለጨረታው የሚያስፈልጉ መስፈርቶች**

1. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው የዘመኑን ግብር የከፈለ እና የዕቃ አቅራቢዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያለው እና የቫት ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
2. ተጫራቾች በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከጨረታው ሰነዳቸውጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመለብር 200 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመክፈልከ ት/ቤቱ ፋይናንስ የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኢንፈሎፐ ማስታወቂያው ከወጣበት እለት ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት በት/ቤቱ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን በ10፡00 ሰዓት ታሽጎ በእለቱ 10፡30 ሰዓት በት/ቤቱ አዳራሽ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ናሙና (sample) ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን የተሟላ የፍላጎት መግለጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል
7. ተጨራቾችን የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ጥቅል ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ተቀባይነት የለውም
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል
10. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11. የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዣ በሲፒኦ በጥቅል 5000/አምስት ሺ ብር/

**አድራሻ፡-**ከተክልሃይማት አደባባይ ወደ ቴድሮዎስ አደባባይ ወደ ሚወስደው መንገድ ደቀ ማሐሪ ሆቴል ፊት ለፊት

**ስልክ ቁጥር** 0111 11 81 26/0118 62 56 07

**የደጃ/ዘርዓይ ደረስ አንደኛና መካከለኛ ደረጃና የጎላ ብርሃን ቅ/መደበኛ ት/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090205501 በአቶ ስሜነህ ያየህ ይማም ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 26/06/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ፅዮን የሺጥላ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 035672 የሴሪ ቁጥር 034981 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ/ሜ መኖሪያ ቤት የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወመ10/20138/18 በቀን 01/07/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ለ/ኩ/8/6/4/24/152540/00 ሴሪ ቁጥር 1670984 በአልማዝ ከበደ ይመር ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ፅ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ሁለተኛ ዙር የተለያዩ ዕቃዎችን በግልፅ ጨረታ አውጥቶ ከዚህ በታች ያሉትን እቃዎችን መግዛት ይፈልጋል።

ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዢያ በባንክ የተረጋገጠ cpo በየሎቱ

1. ሎት 1. አላቂ የቢሮ እቃዎች ........................ 15000 (አስራ አምስት ሺ ብር)
2. ሎት 2. የጽዳት፣ የደንብ ልብስና የስፖርት ትጥቅ ዕቃዎች ........ 5000 (አምስት ሺ ብር)
3. ሎት 3. ቋሚ ዕቃዎች ........................ 8000 (ስምንት ሺ ብር)
4. ሎት 4. የኤሌትሮኒክስ ዕቃዎች ........................ 15000 (አስራ አምስት ሺ ብር)
5. ሎት 5. የጥገና ሥራዎች ........................ 3000 (ሶስት ሺ ብር)
6. ሎት 6. የመኪናና የሞተር ጎማዎች ........................ 5000 (አምስት ሺ ብር)
7. ሎት 7. መስተንግደ ግዥ ------------------------ 5000 (አምስት ሺ ብር)
8. ሎት 8. አዳራሽ ዲኮር የወንበር ዲኮር ------------ 5000 (አምስት ሺ ብር)
9. ሎት 9. የህትመት ስራዎች------------------------ 5000 (አምስት ሺ ብር)
10. ሎት 10. የትራንስፖርት /መጓጓዣ/------------------ 5000(አምስት ሺ ብር)

ብቃት ያላቸዉንና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል በዚህ መሰረት

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው የተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላችሁ የዘመኑን ግብር የከፈሉ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገፅ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር ላይ የተመዘገቡ፣ ቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከጨረታ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል በቀድሞው ን/ስ/ላ/ክ/ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር በአሁኑ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 501 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኢንቨሎፕ ማስታወቂያ ከወጣበት እለት ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት በፋይናንስ ቢሮ ቁጥር 501 ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስራ አንደኛ ቀን በ 4:00 ሰአት ታሽጎ በእለቱ ከቀኑ 4:30 ሰዓት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 501 ይከፈታል። የመክፈቻ ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰአት ታሽጎ ይከፈታል
6. ተጫራቶች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ሎት1፣ ሎት2፣ እና ሎት7 ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን ለሎት3፣ ለሎት4 እና ለሎት 5 በቀረበው እስፔስፐኬሽን መሰረት የተሟላ እስፔስፐኬሽን ማዘጋጀት እና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ያለቫት እና ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. የዘገ የጨረታ እና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
10. የጨረታ አሸናፊ እንደሆኑ ከተለየ ቦሃላ አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ 10 ፐርሰንት ውል ማስከበሪያ በባንክ የተመሰከረ cpo ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ ጥያቄ**

አድራሻ አዲስ አበባበ ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር ከሳር ቤት ወረድ ብሎ ሀረር ክሊኒክ ፊት ለፊት 300 ሜትር ገባ ብሎ ሲሆን የመስሪያ ቤቱ ስልክ ቁጥር 0113834260

**የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት**

---

አቶ ቅደም ተስፋዬ ወ/ሰማያት ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/126/8/4/115672/00 የሴሪ ቁጥር 0146210 ወረዳ 10 የቦታው ስፋት 72 ካ.ሜ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና አቶ ቅደም ተስፋዬ ወ/ሰማያት ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/126/8/4/115672/00 የሴሪ ቁጥር 0146210 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ መሆኑን ያመለከቱ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያለን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ኩብራ ያሲን ሽፋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000101002680 የሴሪ ቁጥር R 097195 በቀን 08/05/2015 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝይቻለው/ይዥዋለው/ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በሴሪ ቁጥር R 085108 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000010301060 በወ/ሮ ዋጋዬ ተስፋዬ ነበረኝ ስም በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የተሰጣቸው የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የጠፋብን በመሆኑ ምትክ ይሰጠን በማለት ያመለከቱ በመሆኑ ይኸው የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በእኔ እጅ ይገኛል ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በአየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 1381/2017 አንቀፅ 36 (3) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ እንዲያመለክት ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ንጉሴ ሃ/ማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 05452/A/1 የሴሪ ቁጥር 0638765 የይዞታ ስፋት 200 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወመ10/19791/18 በቀን 26/06/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/15/64/1/2/04/00 ሴሪ ቁጥር 07163385 በሰዓዳ ይማም መሀመድ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ13/14951/08 ሴሪ ቁጥር 105022 በአቶ አረጋ ታረቀኝ አገኘሁ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ2/49/2/9/257/00 ሴሪ ቁጥር 012753 መልካሙ ጃለታ ዲሬ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በእነ መድሃኒት ንጉሴ ወ/ማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 014988/2/A/B የሴሪ ቁጥር 0129565 የይዞታ ስፋት 204.29 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወመ10/16541/18 በቀን 15/05/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ መለያ ቁጥር 002/2018 ዓ.ም

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ለ2018 በጀት አመት ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያስፈልጉ

ሎት 1. አላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 2000

ሎት 2. አላቂ የፅዳት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10000

ሎት 3. የደንብ ልብስ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000

ሎት 4. የኤሌክትሮኒክስ ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ ብር ስገቡትን ዋጋ 2%

ብቃት ያላቸውን በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

**በዚህም መሰረት**

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታዳሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤ በመንግስት ግ/ን/አ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፤ የቲን ነምበር ያላቸው፤ ቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ /ሲ.ፒ.ኦ/ ከጨረታው ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 5 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት እለት አንስቶ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ግዢ ክፍል ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ኦሪጅናልና ኮፒ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስረኛው ቀን በ11፡00 ሰአት ታሽጎ በማግስቱ ከቀኑ 4፡30 በት/ቤቱ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የባአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ሰአት ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ዕቃዎች ናሙና ለተጠየቀባቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
8. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያቤት ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ለጨረታ ከቀረቡት ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ት/ቤቱ እስከ 20% ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
11. መስሪያ ቤቱ የተሸለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ ማብራሪያ**

- መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት
- ስልክ ቁጥር 0115577296 /0115579044
- አድራሻ፡- ልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ገባ ብሎ

**በል/ክ/ከ/ት/ጽ/ቤት/የመስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

---

በልደታ ክፍለ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 23 ቀበሌ 13 በአሁኑ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 2161 በአልማዝ ከበደ መንግስቱ እና ዶ/ር መንግስቱ ውቤ በተቋማችን የይካተትልኝ አገልግሎት ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ጠያቄ ያቀረቡበት ይዞታ በሲ.አይ.ኤስ መረጃ ላይ በቤት ቁጥር 9999/1 በፈለቀ በላይነህ ስም የተመዘገበ በመሆኑ በደንቡ 163/2016 አንቀጽ 59(1) ላይ በተቀመጠው አግባብ አገልግሎት ለጠየቁት ግለሰቦች መስተንግዶ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ይመለከተኛል ወይም በእዳ፣ በዋስትና፣ በሌላ መልኩ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በልደታ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎት እና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት በፍ/ቤት በማሳገድም ሆነ ወይም በሌላ አግባብ ተቃውሞ እንድታቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ቀርቦ ተቃውሞ (ይገባናል የሚል ጥያቄ) የሚያቀርብ ወገን ከሌለ በመመሪያው መሰረት የግዴታ ውል በማስገባት አገልግሎት ለጠየቁት ሰዎች የይካተትልኝ አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የልደታ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ16/150/8965/00 ስም ሴሪ ቁጥር 128976 በዶ/ር ወልደሀና ክንፈ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፤ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## ግልፅ ጨረታ ማስታወቅያ
## የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ገ/ጉ/ጤ/ጣ/ግ/ጨ/003/2018 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ጤና ፅ/ቤት የገላን ጉራ ጤና ጣቢያ የ2018 ዓ.ም በጀት አመት ሎት 1፣ ቋሚ እቃ ሎት 2፣ ደንብ ልብስ ሎት 3፣ ልዩ ልዩ ማሰሪያዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሰረት ተጫራቾች**

1. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፣ የቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡ ጥቃቅንና አነሰተኛ በራሳቸዉ ሰርተዉ ለሚያቀርቡ እቃዎች ብቻ የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ኖርባቸዋል፡፡
2. ተጨራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች የሚወዳደሩበት በመለየት ፖስታ ላይ በመግለፅ አሽገዉ ኦሪጅናልና ፎቶ ኮፒ ብለዉ በመፃፍ ለይተዉ የድርጅታቸዉን ማህተም እና ፊርማ በማድረግ በጤና ጣቢያው የግዢ ቡድን ቢሮ ቁጥር -405- ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ይህ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት አየር ላይ የሚዉል ሲሆን የጨረታዉን ሳጥን በ11ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ላይ ታሽጎ በዚሁ ቀን ከጠዋት 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት የሚከፈት ስሆን ምናልባት 11ኛዉ ቀን የህዝብ በዓል ወይም ከመንግስት የስራ ሰዓት ዉጭ ከሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት የሚከፈት የሆናል፡፡
5. የጨረታ ማስከበሪያ (በባንክ የተመሰከረለት ቼክ ወይም CPO መጨረሻ ተመላሽ የሚሆን ከጠቅላላ ድምር ብር ላይ ብር 2% ማስያዝ/ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፅዉ ሙሉ ዝርዝር ሁኔታ የጨረታዉ መመሪያ ሆኖ ችግሮች ካጋጠሙ በግዜዉ መመሪያ የሚዳኝ ይሆናል፡፡
7. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፈባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መስራ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. ተጨራቾች ሙሉ ሰነዱን ካልመለሱ ከጨረታ ውጪ ይሆናሉ፡፡
9. የጨረታ ማስከበርያ CPO ሎት 1፡ 10000 ሎት 2፡ 6000 ሎት 3፡ 1000 በዚ ልክ እንድያስገቡ፡፡
10. የጨረታ ዋጋ የሚሞላው በተቀመጠለት መለኪያ ብቻ ስሆን ከመለኪው ውጪ የተሞላ ዋጋ እንዲሁም ስርዝ ድልዝ ወይም በፍሉድ የተነካካ ዋጋ ሙሉ በሙሉ ከጨረታ ውድቅ ይደረጋል፡፡
11. ተጨራቾች ለሚጨራቱት እቃዎች ሙሉ በሙሉ ናሙና ማቅረብ እና በሚያቀርቡት ናሙና ላይ ምልክት ወይም ድርጅቱን የሚገልጽ ምልክትም ሆነ ማህተም ማዳረግ የለበትም፡፡ ተጨራቾች ከሚያቀርቡት ናሙና ከሚያስገቡት እቃ ጋር ፍጹም የተለየ መሆንየ ለበትም፡፡
12. ጨራታውን አሻነፍ ሆነው ከተገኙ ቦኃላ 10% በሸነፉት እቃ መጠን የውል ማስከበሪያ ማስያዣ ይኖርባቸዋል፡፡
13. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታዉን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡ በተጨማሪ ለማብራሪያ ጥያቄ ለጨረታው ከቀረቡ የእቃዎች ዝርዝር ውስጥ መ/ቤቱ እስከ 25 በመቶ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ**

በስልክ ቁ. 0901259401 /0975995034 ደዉለዉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**አድራሻ፡-** ወረዳ 10 አደባባይ ገባ ብሎ

**በአቃ/ቃ/ክ/ከ/ወ10 ገላን ጉራ ጤና ጣብያ**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በወ/ሮ ገነት ማሩ አዱላ ስም በልደታ ክ/ማ የቀድሞ ወረዳ 04 በአዲሱ 03 የቀድሞ ቀበሌ 26 የቤት ቁጥር 1946 በቀን 13/01/1998 የካርታ ቁጥር ል.06.34/122/00 ሴሪ ቁጥር 005473 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአበራ ገበየሁ ለጋሱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080600338560325 በሴሪ ቁጥሩ 140764 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርተኞች በፆም ወቅት

**በሳህሉ ብርሃኑ**

"ጉሮሮ ሲደርቅ፣ ሆድ ሲጮህ... እግር እንዴት ይሮጣል?" ለሚለው ጥያቄ ምላሹ ያለው ሜዳ ላይ ነው። ለብዙዎች ፆም የእረፍትና የዝግታ ወቅት ሲሆን፣ ለፕሮፌሽናል ስፖርተኞች ግን የሰውነትን ወሰን የሚፈትኑበት ጊዜ ነው። "ፆምና ስፖርት የማይገናኙ ናቸው" የሚለው አስተሳሰብ ዛሬ ታሪክ ሆኗል። ይልቁንም ፆም የስፖርተኛውን አእምሯዊ ጥንካሬ እንደሚጨምር ማረጋገጫ ከመስጠቱም በላይ በረመዳን ወቅት ሙስሊም ስፖርተኞች የሚያሳዩት ድንቅ ብቃት ለሌላ ምርምር ጭምር በር የከፈተ ሆኗል።

በዚህ አምድም የረመዳን ፆም በስፖርቱ ዓለም የፈጠረውን አዲስ ባህልና ህግ፣ ተጫዋቾች በረሃብና ጥማት ውስጥ ሆነው እንዴት አስደናቂ ብቃት እንደሚያሳዩና ሜዳ ላይ የሚፈጠሩ ልብ የሚነኩ ገጠመኞችን British Journal of Sports Medicine፣ 'Fasting and Sport Performance' በሚል ርዕስ ያወጣውን ጥናትና ሌሎች ምንጮችን ዋቢ አድረገን እንቃኛለን።

መነሻችንን የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ እናድርግ፤ በዚህ ሊግ ሙስሊም ተጫዋቾች ከንጋት እስከ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ያላቸውን መንፈሳዊ ግዴታ ከከባዱ የሜዳ ላይ ፉክክር ጋር አጣጥመው በመጓዝ ላይ ይገኛሉ። ሊጉ በዘንድሮው የውድድር ዘመን በ20ዎቹ ክለቦች ውስጥ ከ55 በላይ ሙስሊም ተጫዋቾችን የያዘ ሲሆን፣ እነዚህ ተጫዋቾች ጾማቸውን እየጾሙ ለቡድኖቻቸው ወሳኝ ግልጋሎት በመስጠት ላይ ናቸው።

የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የፀሐይ መጥለቅን ተከትሎ ተጫዋቾች ውሃ በመጠጣት አልያም መለስተኛ ምግብ በመውሰድ እንዲያፈጥሩ አጭር ይፋዊ እረፍት እንዲሰጥ ይፈቅዳል፡፡ ፕሪሚየር ሊጉ ጾም ላይ ላሉ ተጫዋቾች ህይወትን ቀላል ለማድረግ "ተፈጥሯዊ እረፍት" የሚል ፕሮቶኮል ተግባራዊ ስለማድረጉም የስካይ ስፖርት መረጃ ያሳያል። ለ2025/26 የውድድር ዘመን፣ ዳኞችም ግልጽ የሆነ የጨዋታ እቅድ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ፀሐይ ስትጠልቅ ወይም ኢፍጣር ሲደርስ ተጫዋቾች ወደ ሜዳው ዳር በማምራት መጠጥ ወይም መለስትኛ ምግብ እንዲመገቡ ይደረጋል። ለዚህም የቡድን አንበሎች ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ለዳኞቹ ቅድሚያ ማሳወቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ተጫዋቾችም ከአንድ ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ አፍጥረው ይመለሳሉ፡፡

ከአርሰናል እንደ ዊሊያም ሳሊባ፣ ከሊቨርፑል መሐመድ ሳላህ፣ ኢብራሂማ ኮናቴ እና ሁጎ ኤኬኬ እየፆሙ ይጫወታሉ። በማንቸስተር ሲቲ ራያን አይትኑሪ፣ ራያን ቼርኪ፣ ኦማር ማርሙሽ እና አብዱኮድር ኩሳኖቭን ጾመኛ ሆነው ሜዳ ይገባሉ፡፡ በማንቸስተር ዩናይትድ እንደዚሁ አማድ ዲያሎ፣ ኑሰይር መዝራዊ እና ግብ ጠባቂው አልታይ ባይንድይር የሚጾሙ ተጫዋቾች ናቸው፡፡

የቀድሞዎቹ አሰልጣኞች ፆመኛ ተጫዋቾችን 'አትጹሙ' ብለው ያስገድዱ ነበር። አሁን ላይ ግን እንደ ቀድሞ የሊቨርፑል የርገን ክሎፕ ያሉ ታዋቂ አሰልጣኞች ለተጫዋቾቻቸው ያላቸውን ክብር በተግባር አሳይተዋል፡፡ የክለቡ ድረ ገጽ መረጃ እንደሚያሳየው ክሎፕ ሊቨርፑል በነበሩበት ወቅት መሐመድ ሳላህና ሳዲዮ ማኔ ፆመው እንዲጫወቱ ክለቡ ልዩ የምግብ ባለሙያና የጸሎት ቦታ በማዘጋጀት ያደረገው ድጋፍ ለሌሎች ክለቦች አርአያ ሆኗል። ይህ 'የብዝሃነት ውበት' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በረመዳን ወር ከፆም ሳይስተጓጎሉ ስፖርታዊ ክዋኔዎችን ከሚያደርጉ ስፖርተኞች ጥቂቶቹ

በ2025 የውድድር ዘመን በጀርመን ቡንደስሊጋ የተከሰተውን እናስታውስ። ዋናው ዳኛ ማቲያስ ጀለንቤክ ጨዋታውን በድንገት አቆሙ። ተጫዋቾችና ደጋፊዎች ግራ ተጋብተው ሳለ፣ የሜይንዝ ተከላካይ ሙሳ ኒያካቴ ወደ ሜዳው ዳር ሮጦ ጥቂት ውሃ ጠጣ። ዳኛው ሆን ብሎ ጨዋታውን ያቆመው ለተጫዋቹ ፆም መፍቻ ሰዓት ደርሶ ስለነበር ነው። ኒያካቴ ውሃውን ጠጥቶ ሲመለስ ለዳኛው የሰጠው 'አመሰግናለሁ' የሚል እጅ መጨባበጥ፣ በስፖርቱ ዓለም ውስጥ ካሉ እጅግ ሰውኛና ልብ የሚነኩ ትዕይንቶች አንዱ ሆኖ ተመዝግቧል።

ይህ ትዕይንት በአሁኑ ወቅት በአውሮፓ ታላላቅ ሊጎች የተለመደ 'አስገራሚ ገጠመኝ' ሆኗል። ከአስር ዓመታት በፊት አንድ ተጫዋች ፆመኛ ሆኖ ሜዳ ውስጥ ቢወድቅ 'ለምን ፆምክ?' የሚል ወቀሳ ይቀርብበት ነበር። ዛሬ ግን ታሪኩ ተቀይሯል። የሊቨርፑሉ መሐመድ ሳላህ በሻምፒዮንስ ሊግ ፍፃሜ ዋዜማ ላይ በፆም ሆዱ ልምምድ ሲሰራ ወይም ካሪም ቤንዜማ ቀኑን ሙሉ ሳይበላና ሳይጠጣ ምሽት ላይ በቼልሲ መረብ ላይ ሶስት ግቦችን ሲያዘንብ ስናይ፣ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ጥንካሬ ከአካላዊ ውስንነት በላይ መሆኑን እንረዳለን።

የቀድሞ የሪያል ማድሪድ ኮከብ ካሪም ቤንዜማ በረመዳን ወቅት የሚያሳየው ብቃት ብዙዎችን ያስገርማል። አንድ ጊዜ በሻምፒዮንስ ሊግ ከቼልሲ ጋር ለሚደረግ ወሳኝ ጨዋታ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት ነበር ፆሙን የፈታው። "ሳይበላ እንዴት ይጫወታል?" ተብሎ ሲሰጋ፣ ቤንዜማ በዚያ ምሽት ሶስት ግቦችን በማስቆጠር ዓለምን አስገረመ። ከጨዋታው በኋላ "ፆም የበለጠ ትኩረት እንድሰጥና መንፈሴ እንዲጠነክር ያደርገኛል" ሲል መናገሩ፣ የስፖርት ሳይንቲስቶች ስለ ምግብና ጉልበት ያላቸውን ቀመር ደግመው እንዲፈትሹ አድርጓቸዋል።

በቱርክዬ ሊግ ጨዋታ ላይ ደግሞ ሌላ የሚደንቅ ክስተት ታይቷል። ጨዋታው እየተካሄደ እያለ የመግሪብ አዛን ተሰማ። በዚያ ቅጽበት አንዱ ተጫዋች ቆስሎ ሜዳ ላይ ወደቀ። ቡድኑ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት በሚመስል መልኩ ተሰበሰበ። ነገር ግን ካሜራዎች ቀረብ ብለው ሲያሳዩ፣ ሁሉም ተጫዋቾች በኪሳቸው ይዘውት የነበረውን ቴምር እያወጡ ፆማቸውን ሲፈቱ ታዩ። ያ ጉዳት ተጫዋቾቹ ፆማቸውን እንዲፈቱ የተቀነባበረ ብልህ ዘዴ ነበር።

የዓለም ስፖርት አስተዳዳሪዎች ለፆመኞች ያላቸው አመለካከት ከመቻቻል አልፎ ወደ ደንብ ተቀይሯል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወጡ አስገራሚ ህጎች አሉ። በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ እና በጀርመን ቡንደስሊጋ፣ ጨዋታው በሚካሄድበት ወቅት ፀሐይ የምትጠልቅ ከሆነ፣ ዳኞች ጨዋታውን ለጥቂት ደቂቃዎች እንዲያቆሙ በይፋ ተፈቅዶላቸዋል። ይህ ህግ ተጫዋቾች ሜዳው ዳር ቆመው ፆማቸውን እንዲፈቱ እድል ይሰጣል። አንዳንድ የአውሮፓ ክለቦችም ፆመኛ ተጫዋቾች ካሏቸው የቡድን ልምምዱን ወደ ጠዋት በጣም ቀደም ብሎ ወይም ወደ ምሽት ያዛውራሉ።

የሆላንዱ ፌይኖርድ እግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝ ሩብን ቫን ፐርሲ በክለቡ ውስጥ ለሚገኙ ፆመኛ ተጫዋቾች ድጋፍ የሚሆን አዲስ አሰራር ይፋ ያደረገውም ከሰሞኑን ነበር። አሰልጣኙ ተጫዋቾቹ ኃይማኖታዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማገዝ የልምምድ ሰዓት እና አይነት ላይ ማስተካከያ ማድረጉን ገልጿል። ፆመኛ ተጫዋቾች የሌሊቱን የዒባዳ እና የስሁር ሰዓት ታሳቢ በማድረግ፣ ጠዋት ወደ ልምምድ ሜዳ ዘግይተው እንዲመጡ ተፈቅዶላቸዋል። እንደዚሁም የፆመኞቹ የልምምድ ጫና እና አይነት ከሌሎች ተጫዋቾች የተለየ እንዲሆን ተደርጓል። ይህም ጉልበታቸውን በአግባቡ እንዲቆጥቡ ይረዳቸዋል ነው የተባለው። ቫን ፐርሲ "ቀኑን ሙሉ ሳይመገቡ መዋል ቀላል አይደለም" በማለት የተጫዋቾቹን ጥንካሬ አድንቆ፣ ክለቡ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አረጋግጧል። ይህ ውሳኔ ቫን ፐርሲ ለተጫዋቾቹ ስነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ብቃት ያለውን ጥንቃቄ የሚያሳይ እንደሆነ ስፖርታዊ ተንታኞች እየገለጹት ይገኛሉ።

በእርግጥ አንድ ስፖርተኛ ሳይበላና ሳይጠጣ 90 ደቂቃ ሙሉ ሜዳ ላይ መሮጥ የሚችለው በዘፈቀደ ሳይሆን በከፍተኛ የሳይንስ ጥናት ታግዞ ነው። የዘመኑ ስፖርት ሜዲስን ፆመኛ ተጫዋቾች ድካም እንዳይሰማቸው የሚያደርጉባቸው የተለያዩ መንገዶችንም እንደሚጠቀሙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ጾም ለስፖርተኞች በአግባቡ ከተመገቡና የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ካስተካከሉ የጤና ጠቀሜታ እንዳለውም በBritish Journal of Sports Medicine 'Fasting and Sport Performance' ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ ሰፍሯል። በጾም ወቅት የፕሮቲን፣ የካርቦሃይድሬት እና የፈሳሽ (ውሃ) ፍላጎትን በደንብ ማሟላት፣ የሥልጠና መጠኑን መቀነስ እና በቂ ዕረፍት ማድረግ የጡንቻ ጥንካሬን ለመጠበቅና የጉልበት ማጣትን ለመቀነስ ወሳኝ ነው። አሁን ላይ ትልልቅ ክለቦች የተጫዋቾችን መንፈሳዊ ፍላጎት የሚያውቁና ከአመጋገብ ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት የሚሰሩ አማካሪዎችን መቅጠር ጀምረዋል።

ፆምና ስፖርት ሲነሳ በአብዛኛው ትኩረቱ እግር ኳስ ላይ ቢሆንም፣ በሌሎች ስፖርቶች (በተለይ ከፍተኛ ጉልበት በሚጠይቁት) ውስጥ ያሉ ስፖርተኞች የሚያሳዩት ጽናት ይበልጥ አስገራሚ ነው። በአሜሪካ የቅርጫት ኳስ ሊግ (NBA) ውስጥ የሚታወቀው ካይሪ ኢርቪንግ፣ በረመዳን ወቅት ጨዋታዎች ሲኖሩት ፆመኛ ሆኖ ይገባል። በቅርጫት ኳስ ውስጥ ተጫዋቾች በየደቂቃው ወደ ላይና ወደ ታች ይሮጣሉ፤ ይህም ከፍተኛ የውሃ ጥም ያስከትላል።

በአንድ ወቅት ኢርቪንግ ፆመኛ ሆኖ 34 ነጥቦችን ያስቆጠረበት ጨዋታ ነበር። ከጨዋታው በኋላ በሰጠው ቃለ-መጠይቅ "ሰውነቴ ቢደክምም፣ መንፈሴ ግን በብርታት ተሞልቷል፤ ፆም ለእኔ እንደ ነዳጅ ነው" በማለት የገለጸው የብዙዎችን ቀልብ ስቧል። አሁን ላይ የNBA ቡድኖች ለፆመኛ ተጫዋቾቻቸው የቪታሚንና የፈሳሽ መጠንን የሚለኩ ልዩ ዲጂታል ሰዓቶችን (Wearable Tech) በመጠቀም ጤንነታቸውን ይከታተላሉ።

በቦክስ ስፖርት ውስጥ ፆም ትልቅ ፈተና ነው። ምክንያቱም ተጫዋቾች ለውድድር የሚመጥን ክብደት መጠበቅ አለባቸው። ታዋቂው ቦክሰኛ አሚር ካን በረመዳን ወቅት የልምምድ ሰዓቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ለሊት በመቀየር ይታወቃል። እንደ ቤላል መሐመድ ያሉ የዩኤፍሲ (UFC) ተዋጊዎች በፆም ወቅት አፋቸው እንዳይደርቅ የሚጠቀሙት ብልሃት አፍን በውሃ መጉመጥመጥና መትፋት ብቻ ነው። ይህ በራሱ ትልቅ የሥነ-ልቦና ጽናት ይጠይቃል።

የአትሌቲክስ ስፖር እንደዚሁ ፈተናው ይበልጥ ይከብዳል። እ.ኤ.አ በ2012 የለንደን ኦሎምፒክ ከረመዳን ጋር ተገጣጥሞ ነበር። በወቅቱ ከ3 ሺህ በላይ ሙስሊም ስፖርተኞች ተሳትፈዋል። ብዙዎቹ ፆመው የተወዳደሩ ሲሆን፣ ሳይንቲስቶች ባደረጉት ጥናት ፆመኛ መሆናቸው በውጤታቸው ላይ ምንም አይነት አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳላመጣና አንዳንዶቹም የግል ምርጥ ሰዓታቸውን እንዳሻሻሉ ተመዝግቧል።